# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 285 ሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

# ‹‹በቀኝ እጃችን ልማታችንን በማስቀጠል በግራ እጃችን ደግሞ ጠላቶቻችንን በመመከት ኢትዮጵያን ማሳደግ አለብን››

-ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

## • አራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በይፋ ተጀምሯል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- "በቀኝ እጃችን ልማታችንን በማስቀጠል በግራ እጃችን ደግሞ ጠላቶቻችንን በመመከት ኢትዮጵያን ማሳደግ አለብን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) አሳሰቡ፡፡ ከስድስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች የሚተከሉበትን አራተኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በይፋ አስጀምረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) "አሻራችን ለትውልዳችን" በሚል መሪ ቃል የተዘጋጀውን የ2014 አራተኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ትናንት ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ላለፉት ሦስት ዓመታት በስኬት ሲከናወን የቆየው አረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ኢትዮጵያ ትልልቅ ነገሮችን መጀመር ብቻ ሳይሆን የምትጨርስ ሀገር እንደሆነች ለዓለም ያሳየችበት ነው ብለዋል፡፡

በቀኝ እጃችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያን የምንገነባው ትምህርት ቤትን ስንገነባ ነው

## • ለአንድ ተማሪ አንድ ጫማ ፕሮጀክት ይፋ ተደርጓል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የምንወዳትን ኢትዮጵያን ለመገንባት የምንችለው ትምህርት ቤትን ስንገነባ ነው ሲሉ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገለጹ። በኢትዮጵያ ታምርት አገራዊ ንቅናቄ ሥር " አዲስ ለልጆቼ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀው "ለአንድ ተማሪ አንድ ጫማ" ፕሮጀክት ይፋ ተደርጓል።

"አዲስ ለልጆቼ" በሚል ርዕስ በተሰናዳው መርሐ ግብር ላይ ንግግር ያደረጉት አቶ መላኩ አለበል፤ የምንወዳትን ኢትዮጵያን መገንባት የምንችለው ትምህርት ቤትን ስንገነባ ነው። ትምህርት ቤት ላይና ልጆች ላይ ሳንሠራና ትውልድን ሳንገነባ የምንፈልጋትንና ሠላም

ኢትዮጵያ የምንገነባው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ መላኩ አለበል

ፎቶ-ሃይሉ አብርሃ



አቶ ጃንጥራር አባይ











ዶክተር አራርሶ ገረመው አቶ መምሩ ሞኬ

# የይርጋለም ኢንዱስትሪ ፓርክ ለ140 ሺህ አርሶ አደሮች የገበያ ትስስር መፍጠሩ ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ይርጋለም፡-የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከ140 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠሩን የሲዳማ ክልል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለጸ።

የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩን አቅም ለማሳደግ ያለመ ውይይት ትናንትና ተደርጓል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መምሩ ሞኬ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩን አቅም ለማሳደግ ያለመ ውይይት ትናንት በይርጋለም ከተማ ሲካሄድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወደ ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የገቡ አልሚዎችን ከአርሶ አደሮችና ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር በቀጥታ በማገናኘት በቅንጅት እንዲሠሩ ተደርጓል። ወደ ፓርኩ የገቡ አግሮ ኢንዱስትሪዎችም ከ140 ሺህ በላይ ከሆኑ

የይርጋለም ኢንዱስትሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






‹‹የጋምቤላ ከተማ የፀጥታ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ወደ ቀደመው ሰላም ተመልሷል››

-አቶ ኡጉት አዲንግ
የጋምቤላ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ

ገጽ 2

ዜና

# ታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ በሕጉ መሠረት እንዲታረሙ እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ

ሞገስ ጸጋዬ




አዲስ አበባ፡- ታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆና መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ በሕጉ መሠረት እንዲታረሙ እየተደረገ መሆኑን የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን አስታወቀ።

የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዳመነ ዳሮታ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከለውጡ በፊት የነበረው የታራሚዎች አያያዝ በተለይ ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ጋር በተገናኘ በርካታ ችግሮች የሚስተዋሉበት ነው። ታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተጥሶና መሠረታዊ ፍላጎታቸው ሳይሟላላቸው የእስር ጊዜያቸውን ያጠናቅቃሉ። ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆና መሠረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ በሕግ እንዲታረሙ ይደረጋል።

ሀገራዊ ለውጥ ከመጣ በኋላ ታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ መሠረታዊ ፍላጎታቸው በተቻለ መጠን ተሟልቶ ታራሚዎችን የማነጽ ሥራ እንደሚሠራ ኮሚሽነሩ አመልክተው፤ ለውጥ ከመምጣቱ በፊት ማረሚያ ቤት ከኅብረተሰቡ ብዙ የራቀና ተደራሽ አልነበረም፤ እንዲሁም መልካም ስም አልነበረውም ብለዋል።

ብዙ ጊዜ ማረሚያ ቤት የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት የማይጠበቅበትና አስፈላጊ ነገሮች የማይሟሉበት እንደነበር አውስተው፤ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ታራሚዎች በትክክል የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው። ወደ ኅብረተሰቡ በሚቀላቀሉበት ወቅት በትክክል አርአያ እንዲሆኑ ከፍተኛ ሥራዎች መሠራታቸውን ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ከአራት ዓመት በፊት ታራሚዎች የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ወደ ኅብረተሰቡ በሚቀላቀሉበት ጊዜ ምንም አይነት የባህሪ ለውጥ እንደማያመጡና በአንጻራዊነት አንድ ታራሚ በተደጋጋሚ ወንጀል ሠርቶ ወደ ማረሚያ ቤት ይገባል። ከለውጡ ማግስት ጀምሮ መንግሥት የፍትህ ተቋማት እንዲሻሻሉ ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረው የፌዴራል ማረሚያ ቤት ይህን በመረዳት በፍጥነት ወደ ለውጥ ጎዳና ገብቷል፤ ለውጥም አምጥቷል። መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት በማካሄድ ደረጃውን የጠበቀ ማረሚያ ቤት እንዲኖር ግንባታ ጀምሯል።

ታራሚዎች ያለባቸውን የስነልቦና ጫና ለማስተካከል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነልቦና የትምህርት ክፍል ጋር በመተባበር እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ማረሚያ ቤቶች የራሳቸው የሆነ የስልጠና ተቋም እንዲኖራቸው በመንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ነው፤ ይህም በቀጣይ ታራሚዎች የስነልቦና ጫና ሳይደርስባቸው ታርመው እንዲወጡ ያስችላል ብለዋል።

ታራሚዎች በዘመናዊ ግብርናና ኢንዱስትሪዎች እንዲማሩና ልምድ እንዲቀስሙ በማድረግ የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ ራሳቸውን ችለው እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑንም ኮሚሽነር ዳመነ ገልጸዋል።


ፎቶ፡- እዮብ ተፈራ

## "ኢትዮጵያ ሀገራዊ ዓላማ የሌላቸው ሰዎች እጅ ላይ መውደቋ አሁን ላለንበት ችግር መንስኤ ሆኗል"

\- ሻለቃ ለማ ማሞ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ ሀገራዊ ዓላማ የሌላቸውና የመገንጠል ዓላማን ያነገቡ ሰዎች እጅ ላይ መውደቋ አሁን በየቦታው እያጋጠመን ላለው የልዩነት እና የፅንፈኝነት እንዲሁም አንዱ ሌላውን የመጠራጠር ችግር መንስኤ መሆኑን ሻለቃ ማሞ ለማ ገለጹ፡፡

"የወገን ጦር" በሚል ርዕስ የቀድሞ ኢትዮጵያ ጦር ሠራዊትን አጠቃላይ ሁኔታ የሚዳስስ መጽሐፍ ለንባብ ያበቁትና ለበርካታ ዓመታት ኑሮአቸውን በውጭ ሀገር ያደረጉት ሻለቃ ማሞ ለማ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና አንድነት ለማስከበር በተደረጉ ጦርነቶች ኢትዮጵያውያን ያለ ልዩነት ዋጋ ከፍለዋል፡፡ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ግን ኢትዮጵያ ሀገራዊ ዓላማ የሌላቸውና የመገንጠል ዓላማን ያነገቡ ሰዎች እጅ ላይ በመውደቋ ዜጎች እርስ በርስ እንዲለያዩና በጥርጣሬ እንዲተያዩ በተሠራው ሥራ ኢትዮጵያ በርካታ ፈተናዎችን እንድትጋፈጥ ተገዳለች፡፡

ለሀገር አንድነት ዘብ ሆኖ የቆየው የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት በተሠራበት አሻጥርና በሌሎችም ምክንያቶች በደረሰበት የውስጥ መቦርቦር መሣሪያውን ሲያስቀምጥ ኢትዮጵያ በጠላቶቿ እጅ ወደቀች ያሉት ሻለቃ ለማ፤ አገሪቱን የተረከቡት ሰዎችም ኢትዮጵያዊ መሠረት ስለሌላቸው ፖለቲካውን ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ብሔር ላይ እንዲያተኩር በማድረግ ዜጎች እርስ በርስ እንዲለያዩ መደረጉን አስታውሰዋል፡፡

ዲሞክራሲ ሊመጣ የሚችለው በመደማመጥና በሀሳብ አሸናፊነት ነው ያሉት ሻለቃ ማሞ፤ የሆነ ሰው ከመጣበት ብሔር የተመሠረተ ፓርቲ ካለ ጥሩም ይሥራ መጥፎ ለዛ ፓርቲ ማድላቱ ስለማይቀር ዴሞክራሲ በጽንፈኛ የዘር ፖለቲካ ሊመጣ አይችልም ብለዋል፡፡

ያለፉት መንግሥታት የየራሳቸው መጥፎ ጎን ቢኖራቸውም ሀገራዊ ዓላማ ስለነበራቸው ኢትዮጵያን ማቆየት ችለዋል ያሉት ሻለቃ ማሞ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታየው ችግር ቀዳሚው መፍትሔ መሆን ያለበት ቋንቋንና ባህልን ለማበልጸግ የሚያስችል ሲቪል ድርጅት ማቋቋም እንደተጠበቀ ሆኖ ፖለቲካ ግን ከጽንፈኝነት መጽዳት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

በብሔራቸው በመደራጀታቸው ብቻ ማኅበረሰባቸውን የበላይ ያደረጉ የሚመስላቸው ኃይሎች ይህን በቀላሉ ላይቀበሉ እንደሚችሉ ያመለከቱት ሻለቃ ማሞ፣ በጉዳዩ ላይ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በውጭ ሀገራት የምንኖር ኢትዮጵያውያን በቀለም፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት በጭራሽ በማንገናኛቸው አገሮች ሄደን መብታችን ተጠብቆ እንኖራለን ያሉት ሻለቃ ማሞ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከአንዱ ክልል ወደ አንዱ ክልል ተዘዋውሮ መሥራት አዳጋች ከሆነ ኢትዮጵያ አደጋ ላይ መሆኗን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍም ክልላዊ አወቃቀሩን ድጋሚ ማጤን እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ እንድትደርስ በርካቶች ያለ ምንም ዘር ልዩነት ዋጋ መክፈላቸውን አስታውሰው፤ የዛሬ ወጣቶችም የሀገርን ጉዳይ የጋራ አጀንዳ አድርገውና ሀገራዊ ራዕይ ኖሯቸው በትብብር የሀገርን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ የቀደምቶቻቸውን ታሪክ ማስቀጠል እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

## ‹‹የጋምቤላ ከተማ የፀጥታ ሁኔታ ሙሉ ስሙሉ ወደ ቀደመው ሰላም ተመልሷል››

-አቶ ኡጉት አዲንግ
የጋምቤላ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ከቀናት በፊት በጋምቤላ ክልል የነበረው ውጊያ ተወግዶ ከተማው ሙሉ ለሙሉ ወደ ቀደመው ሰላም መመለሱን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የጋምቤላ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ኡጉት አዲንግ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክልሉ ሕዝብ ሰላም ወዳድ በመሆኑ ከጥቂት ቀናት በፊት ከጠላት ጋር የነበረውን ውጊያ በማሸነፍ በአሁኑ ሰዓት የጋምቤላ ከተማ የጸጥታ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ወደ ቀድሞው ሰላማዊ ሁኔታ ተመልሷል።

በክልሉ ያሉ የመንግሥት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ወደ ቀደመ ሥራቸው ተመልሰው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል ያሉት ኃላፊው፤ የአውሮፕላን በረራን ጨምሮ የትራንስፖርት አገልግሎት በሙሉ ወደ ሥራ ገብተዋል ብለዋል።

እንደ አቶ ኡጉት ገለጻ፤ በጋምቤላ ከተማ የባጃጅ ትራንስፖርትም በስፋት አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው። ምግብ ቤቶችና የንግድ ተቋማት በተመሳሳይ ወደ ቀደመ ሥራቸው በመመለስ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

በአሁኑ ጊዜ በክልሉ የገበያ ቦታዎች ክፍት ሆነው ኅብረተሰቡ በመገበያየት ላይ ይገኛል ያሉት ኃላፊው፤ መሰል የንግድ እንቅስቃሴዎችም ክፍት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በቀጣይ በክልሉ መሰል ችግር እንዳይደገም ለማድረግ ከውጭና ከውስጥ ያሉ የጠላት ሰንሰለቶች እንዲጋለጡ ለማድረግ ምርመራ ከማድረግ በተጨማሪ ከኅብረተሰቡ ጋር ውይይት እየተካሄደ ነው ብለዋል።

በሌላም በኩል ክልሉ እንዳይረጋጋ የሚፈልጉ ጥቂት አካላት የማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅመው ክልሉ ላይ ያልተከሰቱ ነገር ግን በሬ ወለደ ወሬዎችን እያወሩ ኅብረተሰቡን እያሳሳቱ በመሆኑ ኅብረተሰቡ በውሸት ወሬዎች ሳይደናገር መደበኛ ሥራውን እንዲያከናውን አሳስበዋል።

በውሸት የሚሰራጩ መረጃዎች እስኪጠሩ ኅብረተሰቡን በማወያየት የማጋለጡ ሥራ ይቀጥላል ያሉት ኃላፊው፤ ከሰሞኑን በክልሉ በነበረው ችግር ኅብረተሰቡ አንድ በመሆን ጠላትን ማሸነፍ ችሏል ብለዋል።

ከዚህ በኋላም ጠላት ችግር ወደ መፍጠር ተግባር ይገባል የሚል እምነት ባይኖርም ቀጣይም ኅብረተሰቡ አንድ በመሆን ጠላትን ተከታትሎ ማጋለጥ እንዳለበት አቶ ኡጉት አሳስበዋል።



# “ኢትዮጵያን ለመረዳት በሙሉ አይታ መመልከት ይገባል”

-አቶ ደስታ ሌዳሞ
የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

ወርቁ ማሩ

ሀዋሳ፡- የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ለመገንዘብ በጎዶሎ ሳይሆን በሙሉ እይታ መረዳት እንደሚገባ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አስታወቁ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሀዋሳ ከተማ ባዘጋጀው “ስለኢትዮጵያ” የተሰኘ የፓናል ውይይት ላይ እንደገለፁት፤ አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያን ብልጽግና ይጠራጠራሉ፤ ትፈርሳለች ብለው የሚያስቡም አሉ፤ ይህ አስተሳሰብ ኢትዮጵያን በሙሉ እይታ ባለመመልከታቸው ከተሳሳተ እይታ የሚመነጭ ነው፡፡

አንዳንድ የኢትዮጵያ ጠላቶች ኢትዮጵያውያን አንድ ስላልሆኑ ብንገፋቸው በቀላሉ ይወድቃሉ ብለው ስለሚያስቡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለመበታተን ሌት ተቀን ይሠራሉ ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ ነገር ግን ደፍረዋት መልሰው ሲወድቁ ይታያሉ ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት ያጋጠሟትን ፈተናዎች ተቋቁማ ስትሻገር ኖራለች፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አንግቦ


ፎቶ - ዳኜ አበራ

የተነሳው “ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች” የሚለው መሪ ሃሳብም ይህንን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በርካታ ውጣውረዶችን እየተጋፈጠች ቢሆንም በርካታ መልካም እድሎችና አጋጣሚዎች ያሏት በመሆኑ እነዚህን በሚዛኑ ማየት ኢትዮጵያ ወዴት እየሄደች ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ እንደሚሰጥ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ደስታ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለው የሀገር ግንባታ ሂደት በአዲስ ምዕራፍ፣ በአዲስ አተያይ፣ በአዲስ ፍኖተ ካርታ፣ በአዲስ ሜዳ እየተጓዘ በመሆኑ ለዚህ ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋፅዖ ማበርከት አለብን፡፡

የሀገር ግንባታ ሂደት በራዕይና በግብ ሲመራ በአጭር ጊዜ ውጤት የሚገኝበት ይሆናል ያሉት አቶ ደስታ፤ ከዚህ ውጭ ግን ብንዳክር የምንፈልግበት ጫፍ ላይ ልንደርስ ስለማንችል ግባችንን እያሰብን ልንሠራ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ግባችንን ለማሳካትም ያሉትን መልካም እድሎችና መልካም አጋጣሚዎች ልቅም አድርጎ መያዝ፤ ፈተናዎችን መለየት እና በዚያ ላይ መሥራት እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያቀረበው የፎቶ ኤግዚቢሽን ኢትዮጵያ የመጣችበትን ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ደስታ፤ ላለፉት መቶ ዓመታት የነበሩት ፈተናዎችና እነዚህን እንዴት እየፈታች እንደመጣች የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ደስታ እንደገለጹት፤ ለውጥ በባህርይው ጊዜ የሚፈልግ ተግባር ነው፡፡ በዚህ የተነሳ እዚህ እዚያም የሚሰሙ ድምጾች አሉ፡፡ እነዚህ በለውጥ ውስጥ የሚከሰቱ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ለዚህ ተባብሮ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

ኢትዮጵያ የምትገኝበት ስፍራ ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያለበት በመሆኑ የኢትዮጵያን ትንሳኤ የማይፈልጉ ኃይሎች ሲፈታተኗት ኖረዋል፤ ይህ ደግሞ በርካታ ቀውስ የፈጠረ ፈተና ነው፡፡ ሆኖም በእነዚህ ሁሉ ፈተናዎች ውስጥ ኢትዮጵያ እንዴት መቆም ቻለች የሚለው በደምብ ሊፈተሽ እንደሚገባውም አቶ ደስታ አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም እያለፍን ያለነው በዚህ ሂደት ውስጥ በመሆኑ የኑሮ ውድነት፤ የሰላም እጦት እና መሰል ፈተናዎች አሉ፡፡ በአንጻሩ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥም ብዙ ድል ተመዝግቧል፤ ፈተና፣ እድልና ተስፋ ያልነውም ለዚህ ነው ብለዋል፡፡

# በሕወሓት የተፈተነው ኢንጂነር ውጣ ውረድ

ውብሸት ሰንደቁ

ወህኒ፣ ዛቻና እንግልት የግድያ ሙከራና የ“ኧረ ባክህ ተው” ምልጃ የተፈራረቁበት ሰው ነው:: የስደትና ሽሽት ገፈትን ቀምሶ በርካታ የበረሃ መንገዶችን በእግሩ ኳትኗል:: ከመንግሥትም ሆነ ከአንዳች ቡድን ጋር የሚያጋጨው የግል ጉዳይ ግን አልነበረውም:: ነገር ግን የሕወሓት ግፍና መከራ ለእምቢተኝነቱ ምክንያት ሆነውታል::

እንኳን ሕወሓት አፍንጫ ሥር ተቀመጦ ይቅርና መሐል ሀገር ሆኖ የፍትሕና የዴሞክራሲ ጥያቄ ማንሳት ከማይቻልበት ከዛሬ 14 ዓመት በፊት ነበር በትውልድ ቀዬው እየተከሰተ የነበረውን የሕወሓት አገዛዝ በግልፅ በመቃወም የፖለቲከኝነቱን ጎራ የተቀላቀለው::

ኢንጂነር የማነ ሃይሌ ይባላል:: በሕግ ማስከበሩ ወቅት በትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ ሆኖ ሠርቷል:: ትውልድ እና ዕድገቱ ሽራሮ ሲሆን በዚያው ቦታ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማረው:: ከአክሱም ዩኒቨርሲቲ በሲቪል ኢንጅነሪንግ የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዟል:: ሁለት ልጆችም አሉት::

ኢንጂነር የማነ ፖለቲከኛና ከአረና ትግራይ መሥራቾች አንዱ ነው:: በጊዜው የነበረው ምርጫ ውድድር ባይባልም እንኳን ለሁለት ጊዜ ያህል ለፓርላማ ተመራጭነት ተወዳድሯል:: ብዙ መስዋዕትነት የነበረበት ውድድር ነበረ ይላል ኢንጂነር የማነ::

ሕወሓት ተወዳዳሪ የማይፈልግ አካል ነበር የሚለው ኢንጂነር የማነ፤ በተለይ ለሕወሓት፣ አረና ትግራይ ማለት በወቅቱ የሕዝብና የሀገርን ጉዳይ በወግ ተገንዝቦ የሚወዳደር ፓርቲ ስለነበር በጠላትነት የሚፈረጅ ፓርቲ ነበር::

በምርጫ ወቅት ዛቻን ጨምሮ በርካታ ጫናዎች እንደደረሰበት እንዲያውም ከዚያም አልፎ ሽራሮ ታህታይ ዓደይአቦ የምርጫ ክልል ላይ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ማግሥት የግድያ ሙከራም እንደተደረገበት ይናገራል:: አብረውት ለምርጫ ከተወዳደሩትም የሕወሓት ደጋፊ ያልሆኑ ሰዎች ተገድለዋል::

በወቅቱ ዴሞክራሲ በቲዎሪ ብቻ ነበር ያለው፤ እኛ ደግሞ ዴሞክራሲን በተግባር እንፈልግ ነበር የሚለው ኢንጂነር የማነ፤ በአጠቃላይ ሕወሓት፣ ሕወሓት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የኢሕአዴግን ሥርዓትም አጥብቄ እቃወም ነበር ሲል ይናገራል:: በነበርኩበት ፓርቲም ሆነ በግሌ ያለ ምርጫ ለውጥ


ኢንጂነር የማነ ሃይሌ

ሊመጣ አይችልም የሚል አቋም ስለነበረን ነው ለፍትሕ፣ ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲ ስንታገል የነበረውም ይላል::

በትግሉ ወቅት የኢሕአዴግ አባላት እና የደኅንነት ሰዎች እዚህ አገር ዴሞክራሲ የሚባል ነገር የለም እያሉ በግልፅ እየነገሩን ከዚህ ትግል እንድንታቀብ ይለምኑንና እንዳንዴም ሊያስፈራሩን ይሞክሩ ነበር:: በሕይወት መኖር አትፈልጉም ወይ ሁሉ እንባል ነበር:: በዚህ ዙሪያ ዝም በል ማለታቸው የፖለቲካ ትግልህን አቋርጥ እና ሕዝቡን እንደፈለግን እናድርገው ማለታቸው ስለሆነ በፍፁም በእኔ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም ይላል የማነ:: በዚህ ምክንያትም ለእስር እና ለእንግልት ተዳርጓል፣ እንዲሁም ተደጋጋሚ የግድያ ሙከራ ተቃጥቶበት አምልጧል::

ሕወሓት ትምክህተኛ፣ ፍፁም ፀረ ሕዝብና ፀረ ዴሞክራሲ ቡድን ነው የሚለው የማነ፤ በሕወሓት ዕይታ የትግራይ ሕዝብ ደጋፊ እና ጠላት ተብሎ በሁለት ነው የሚከፈለው፤ ጠላት ተብሎ የተፈረጀው ሕዝብ በፍርሃት እንዲኖርና ምንም ዓይነት ተቃውሞ እንዳይኖረው በተለያየ መንገድ ተፅዕኖ ይደረግበታል ሲል ያስረዳል::

ጦርነቱ በተጀመረበት የውስጥ ጠላትን ለማጥራት በሚል እንዳይገሉት በመሥጋት ወደ ወልቃይት ጠገዴ መሄዱን የሚናገረው ኢንጅነር የማነ፤ ጠገዴን የአማራ ልዩ ኃይል እና ፋኖ ሲቆጣጠር መታሰሩንና ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ ይዞ ስለነበር መለቀቁን ከዚያም እንደገና ወደ ትግራይ መመለሱን ይገልፃል:: በወቅቱ ሽሬ እና አካባቢውን የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ተቆጣጥሮት ስለነበር የአማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ ከጠገዴ እስከ ተከዜ በመኪና ካደረሰው በኋላ በደደቢት በኩል በእግር ተጉዞ ወደሽሬ አቅንቷል::

ከዚያም መንግሥትም ለጊዜያዊ መስተዳድር ጥሪ አቅርቦ ስለነበር ወደሰሜን ምዕራብ ዞን ተልኮ በምክትል አስተዳዳሪነት ሥራ ጀመረ:: በሰሜን ምዕራብ ዞን በምክትል አተዳዳሪነት ሥራ ላይ እያለ የግድያ ሙከራ ተደርጎበት ራሱን ተከላክሎ አምልጧል::

በወቅቱ ሕወሓት አካባቢውን ቢለቅም ተላላኪዎቹ ስላልፀዱ እና በዘረጋው ኔት ወርክ ስለሚሠራ እርምጃ የሚወሰድባቸውን ሰዎች ሥም ዝርዝር እየለጠፈ ሕዝቡን ያሸብር ነበር የሚለው የማነ፤ የፀጥታው ጉዳይ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የተሰጠ ጉዳይ ሆኖ እኛ ስንሠራ የነበረው ሕዝቡ የባሰ ጉዳት እንዳይገጥመው የሚያደርጉ የሲቪል ሥራዎችን ነው ብሏል::

በጊዜያዊ አስተዳደሩ ጊዜ የነበረው የሕዝብ አቀባበል ለመግለፅ የሚቸግር እንደሆነና ጊዜያዊ አስተዳደሩም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በትጋት ሲሠራ እንደነበረ ይገልፃል:: የነበረው ዕርዳታ አቅርቦትም በቂ የሚባል ነበር ይላል:: ነገር ግን ይህ ነገር እንዳይቀጥል የሚፈልጉ አካላት መኖራቸውንና ሕዝቡ ለጊዜያዊ አስተዳደር ይናገር እንደነበር ጠቁሟል::

ኢንጂነር የማነ፤ መንግሥት በሁለንተናዊ መልኩ የተጎዳውን የትግራይ ሕዝብ ተስፋ እየሰጠው እንደሆነ ያምናል:: ክረምት እየገባ ስለሆነ ሕዝቡ ወደ ሰላም እና ወደ እርሻው እንዲመለስ ከሁሉም ጊዜያት የተሻለ የሰላም ጭላንጭል እየታየ ነውም ይላል:: የታየው የሰላም ጭላንጭል ለትግራይ ሕዝብ ትልቅ ተሥፋ፤ በትግራይ ሕዝብ እየተጫወቱ ለሚኖሩ አካላት ፍቱን መድኃኒት ነው ይላል ኢንጂነሩ::

መንግሥት የከፈተውን የሰላም በር የትግራይ ሕዝብ መጠቀም አለበት የሚለው የማነ፤ ሕወሓት ብዙ ጥፋት ስላጠፋ የሰላም አማራጩን ላይጠቀምበት ስለሚችል የትግራይ ሕዝብ፣ ሕወሓት ሰላማዊ አማራጮችን እንዲጠቀም ግፊት ሊያደርግበት እንደሚገባ ይናገራል::

እንደ ኢንጂነር የማነ ገለፃ፤ ሕወሓት ድርድሩን ይፈልገዋል:: የሚፈልገው ስምምነት ለማምጣት ሳይሆን ሕዝቡን ለማታለል ነው:: ድርድሩን መንግሥትን የማንበርከክ አቅም አለኝ የሚል የተለመደ አሉባልታውን ለመንዛት እንደሚጠቀምበት እገምታለሁ::በዚህ መንገድ በማጭበርበር ተጨማሪ ዓመታትን የሚያገኝበትን ዕድል ነው የሚፈጥረው:: ስለዚህ መንግሥት የሰላም አማራጮችን ሲጠቀም ጥንቃቄ ማድረግ አለበት::

# በበጎ ፍቃድ አገልግሎት 30 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን ተገለጸ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡ በክረምት በበጎ ፍቃድ አገልግሎት 30 ሚሊየን ችግኞችን ለመትከል ማቀዱን የኢትዮጵያ ወጣቶች ሰላምና ብልጽግና ተልዕኮ ሊግ ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሰላምና ብልጽግና ተልዕኮ ሊግ ፕሬዚዳንት ወጣት ብርሃኑ በቀለ ሊጉ እስካሁን በሠራቸው ሥራዎች እና በቀጣይ በ2014 በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለመሥራት የታቀዱ ተግባራትን በሚመለከት ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት ዓመት በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ100 ሺህ በላይ የሊጉን አባላት እንዲሁም ሌሎች በጎ ፍቃደኛ ወጣቶችን በማስተባበር 30 ሚሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዷል፡፡

የችግኝ ተከላው በአዲስ አበባ መስተዳድር፣በኦሮሚያ ክልል እና እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ክልሎችም እንደሚከናወን ተናግረዋል፡፡

ከችግኝ ተከላው በተጨማሪ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የአቅመ ደካሞችን ቤቶች ማደስ፣ደም መለገስ፣ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የተደፈኑ የጎርፍ ማስወገጃ ቱቦዎችን የመክፈት ሥራዎች ፣በሆስፒታል እና በጤና ጣቢያ በመገኘት ሕሙማንን መንከባከብ እና መጻሕፍት በማሰባሰብ ለሕዝብ ቤተመጽሐፍት የማስረከብ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ጠቅሰዋል፡፡

ከከፍተኛ ተቋማት የተመረቁ ወጣቶች የዚህ በጎ ዓላማ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ ያቀረቡት የሊጉ ፕሬዚዳንት ማንኛውም የዚህ ዓላማ ተሳታፊ መሆን የሚፈልግ የአዲስ አበባ ወጣት በሊጉ ቢሮ በመገኘት መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን ተናግረዋል፡፡በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ የሚሰሩ ተግባራትም በገንዘብ ሲተመኑ 50 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ እንደሚሆኑ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሰላምና ብልጽግና ተልዕኮ ሊግ ከዚህ ቀደምም የኮቪድ -19 መከላከል ሥራዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ እና በኦሮሚያ ክልል ላይ ትልልቅ ሥራዎችን መሥራቱን ጠቁመው፤ በ6ኛው አገራዊ ምርጫ ከኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ፍቃድ አግኝቶ የመራጮችና የስነ ዜጋ ትምህርትን ለ200ሺህ ዜጎች መስጠቱን አስታውሰዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ላይም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በመሆን ትልቅ ሥራ መስራቱን አስታውቀዋል፡፡

# ድርጅቱ በ19ኛው ዙር ያሰለጠናቸውን የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች አስመረቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በልዩ ልዩ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ዘርፎች በ19ኛ ዙር ያሰለጠናቸውን ባለሙያዎች አስመረቀ፡፡

በርዕሰ አንቀጽ አጻጻፍ፣ በመልዕክት እና አጀንዳ ቀረጻ፣ በጋዜጣዊ መግለጫ አጻጻፍና አደረጃጀት፣ በቪዲዮ ኤዲቲንግ፣ በፎቶ ጋዜጠኝነት፣ በግራፊክ አርት፣ በሌይአውት እና ዲዛይን ዘርፍ ያሰለጠናቸውን 13 የአዲስ አበባ እሳትና ድንገተኛ አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ባለሙያዎችን ትናንት አስመርቋል።

በስልጠናው ማጠቃለያ ላይ መልዕክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ትልቅ ልምድ ያለው አንጋፋ ተቋም ነው። በመሆኑም ይህንን ሀብቱን በመጠቀም በሚዲያ ዘርፍ የልህቀት ማዕከል ለመሆን ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከልን በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ የልህቀት ማዕከል በማድረግ ያካበተውን ልምድ ለሌሎች በማካፈል ለዘርፉ ማደግ ትልቅ ሚና እንዲጫወት እየተሠራ ነው ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ድርጅቱ በማዕከሉ አማካኝነት የተቋሙን አንጋፋና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ጨምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም አካባቢ ያሉ የዘርፉን ባለሙያዎች በመጠቀም እስካሁን ለፌዴራልና ለክልል ተቋማት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ባለሙያዎች በ19 ዙር ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል፡፡

ሥልጠናውን የሚሰጠው ገንዘብ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሚዲያ እንዲያድግና ተቋማትም የሚዲያና ግንኙነት ሥራቸው ስኬታማ እንዲሆን የበኩሉን አገራዊ ድርሻ ለመወጣትም ነው ብለዋል፡፡



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት 82 ዓመታትን ያስቆጠረና በኢትዮጵያ የስነጽሑፍና የጋዜጠኝነት መስክ ትልቅ አሻራ ያሳረፈ አንጋፋ ተቋም መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፍቃዱ፤ ስልጠናው በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ልምድ የተገኘበት ስለሆነ በቀጣይነትም ያለውን እምቅ አቅም ተጠቅሞ የሚሰጠውን ስልጠና አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡

ኮሚሽኑም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን መርጦ ያለውን እውቀትና ልምድ ለመጋራት ሠራተኞችን ለስልጠና ወደ ኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጠና ማዕከል ስለላከ ምስጋና አቅርበው፤ በቀጣይነት አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በስልጠናው የተሳተፉ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከል የወሰዱት ስልጠና ያላቸውን ሙያ ለማሳደግና ሥራቸውንም በእውቀት ላይ ተመሥርተው እንዲሠሩ ትልቅ እድል የፈጠረላቸው መሆኑን ገልጸዋል።

ስልጠናውን የሚሰጡት ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃት፣ የመስተንግዶ አገልግሎቱ፣ የስልጠና አሰጣጡ ሁሉ እጅግ የሚያስደስትና ያለባቸውን ሙያዊ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል አቅም የገነቡበት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስልጠና ማዕከል የዛሬ ሰልጣኞችን ጨምሮ በ19 ዙሮች ከ16 የተለያዩ የፌዴራል፣ የክልልና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቋማት የተውጣጡ 180 የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ባለሙያዎችን አሰልጥኖ አስመርቋል፡፡

## የይርጋለም ኢንዱስትሪ…

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አርሶአደሮች ጋር በፈጠሩት የገበያ ትስስር የግብርና ግብዓቶችን በአቅራቢያቸው ማግኘት ችለዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ የተለያዩ የማር ማቀነባበሪያ፣ ቡናን በዘመናዊ መልክ አዘጋጅተው የሚሸጡና የአቮካዶ ዘይት የሚያመርቱ ፋብሪካዎች መኖራቸውን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል።

በፓርክ ውስጥ ከሚገኙ የአግሮ ኢንዱስትሪ ማምረቻዎች መካከል ሳንቫድ የተባለው የአቮካዶ ዘይት ማምረቻ ፋብሪካ ብቻ ከ88 ሺህ አርሶ አደሮች ጋር የግብዓት አቅርቦትና የገበያ ትስስር ፈጥሯል። ዋይቢኤም የተባለው ሌላኛው የአቮካዶ ዘይት ማምረቻም በበኩሉ ከ44 ሺህ አርሶ አደሮች የሚረከበውን ምርት ተቀብሎ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በተጨማሪ በፓርኩ የሚገኙ የወተት፣ የማርና የቡና ምርት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችም በአካባቢው ከሚገኙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር በግብዓት አቅርቦት ላይ አብረው እየሠሩ መሆኑን የገለጹት አቶ መምሩ፤ በዚህም ከሶስት ሺህ በላይ ለሆኑ አርሶ አደሮች ዘላቂ ገቢ እንደተፈጠረላቸው አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ወደ ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ለመሥራት ጥያቄ ያቀረቡ ኢንቨስተሮች መኖራቸውን የጠቆሙት አቶ መምሩ፤ 21 አልሚዎች ወደ ፓርኩ ለመግባት ጥያቄ አቅርበው ስምምነት መደረጉንም አስታውቀዋል።

ስምምነት ካደረጉት ኢንቨስተሮች መካከል ግንባታ አጠናቀው የፋይናንስ አቅርቦት የሚጠብቁ አሉ። በአንጻሩ የግንባታ ሂደት ያልጀመሩና ሂደታቸው ደካማ የሆኑ አልሚዎች በፍጥነት ግንባታቸውን እንዲያጠናቅቁ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ሂደት ላይ ያሉት ኢንቨስትመንቶችን ወደ ሥራ ማስገባት ሲቻል ተጨማሪ አርሶአደሮች የገበያ ትስስር እንደሚፈጠርላቸው ይታመናል ብለዋል።

የሲዳማ ክልል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የቦርድ ሰብሳቢና የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አራርሶ ገረመው በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በፓርኩ የሚገኙ ፋብሪካዎች ምርት በማሳደግ፣ የገበያ ትስስርን በማስፋትና የምርት ጥራት በማሻሻል ረገድ ተጨማሪ ጥረት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

ኢንዱስትሪ ፓርኩ አሁን ካለው አቅምም በላይ መሥራት የሚችልና ለግብርና ማቀነባበሪያ ምቹ የሆነ አካባቢ ላይ ስለሚገኝ ተጨማሪ አርሶአደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ባለሃብቱም ሆነ የሚመለከታቸው አካላት ይበልጥ መሥራት አለባቸው ብለዋል።

ክልሉ ባለው የፋይናንስ አቅም ኢንዱስትሪ ፓርኩን ይበልጥ ለማደራጀት ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢንቨስተሮችም ወደ ፓርኩ በመግባት የራሳቸውን ሼድ እንዲያለሙና በአካባቢው ያለው የግብርና ምርት በማቀነባበር ለገበያ እንዲያቀርቡ ጥሪ አቅርበዋል።

የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ በ294 ነጥብ ሶስት ሔክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ 11 ሼዶች ተገንብተውበታል። የኢንዱስትሪ ፓርኩ በ2014 ዓ.ም ከአምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ሲያስገኝ፤ ለሰባት ሺህ አንድ መቶ ሠራተኞች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠሩ ተገልጿል።

## ኢትዮጵያን…

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ያለባትን፣ ለዜጎቿ ክብር የምትሰጥ ኢትዮጵያን ልናገኝ አንችልም ብለዋል።

ሚኒስትሩ፤ በቅድሚያ ትምህርት ቤት ላይ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ በመናገር፤ ከዚህ አኳያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለፉት ዓመታት ተማሪዎች ላይ የሥነ ልቦና ችግር እንዳይደርስ፤ በምግብና በአልባሳት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እንዳይደናቀፉ በማድረግ የሠራው ተግባር አበረታች እንደነበር አንስተዋል። የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄውን ለልጆች ከተሰጠው ትኩረት ጋር ማቀናጀቱንም አድንቀዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ የተፈጥሮ ሀብትና ጸጋ ያሏት ሀገር ናት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሁሉንም አይነት ሀብቶች መጠቀም ባለመቻሏ በኋላ ቀርነቷና ድህነቷ ተጠቃሽ እየሆነች ነው ብለዋል። ይህን ችግር ማለፍ የሚቻለው ደግሞ ትምህርት ቤቶች ላይ የጎደሉትን ነገሮች በአግባቡ በመሥራት እንደሆነ የጠቀሱት አቶ መላኩ፤ ተማሪዎችን ከመመገብ ባሻገር በሀገር ውስጥ ምርት አልባሳት እንዲማሩ ማድረጉ በሀገራቸው ምርት እንዲኮሩ ያድርጋል ሲሉም ገልጸዋል። በሀገር ውስጥ ምርትን የማስፋፋት ሥራ በሁሉም መስክ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊው አቶ ጃንጥራር አባይ፤ በኢትዮጵያ ብልጽግና ጉዞ ውስጥ ትልቅ አዎንታዊ ድርሻ ያላቸው ሕጻናትን መንከባከብ እና በትምህርት ገበታቸው እንዲቀጥሉ ማድረግ፤ ደስተኛ ሆነው አዕምሯቸው እንዲበለጽግ ያደርጋል ብለዋል። ለዚህ ደግሞ ልጆችን በሀገር ውስጥ ምርት መደገፍ ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም ጠቁመዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ምግብን ጨምሮ ለተማሪዎች አልበሳትን ሲያቀርብ ከሌሎች መሠረተ ልማቶች ቅድሚያ በመስጠት እንደሆነ የጠቀሱት ምክትል ከንቲባው፤ ይህም የሆነው ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ውስጥ እያጋጠማቸው ያለውን ችግር ለመፍታት እንደሆነ አመላክተዋል።

በዚህ ምክንያት ምግብ እንዲሁም የትምህርት አልባሳትን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳለ ገልጸዋል። ይህ ውጤት የሚለካው በልጆቹ ውጤት አማካኝነት እንደሆነ በመጠቆም፤ ፕሮግራሙ በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥልም አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ አንቺነሽ ተስፋዬ በመድረኩ እንደተናገሩት፤ በተለያየ ምክንያት እጅ አጥሯቸው መግበውና አልብሰው ግብዓት አቅርበው ማስተማር ያልቻሉ ወላጆች እፎይታ አግኝተዋል።

በትምህርት ቁሳቁስ መለያየት ደረጃ እየወጣላቸው በምሳ እቃ ጉራማይሌነት እና ባስ ሲልም በምግብ እጥረት የአቻዎቻቸውን የትምህርት ግብዓትና አልባሳትን ይመለከቱበት የነበረው ጊዜ አልፎ በእኩልነት የልጅነት አዕምሯቸው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ ብለዋል። ተማሪዎችን የመመገቡና በሀገር ውስጥ አልባሳት የማስተማሩ ሂደት ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት “አዲስ ለልጆቿ” የተሰኘ መርሐ ግብር ያካሄደ ሲሆን፤ ሁነቱ የሀገር ውስጥ አምራችና ምርትን የሚያበረታታ፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን የሚያድን፣ ገቢ ምርቶችን የሚተካ፣ በርካታ የሥራ እድሎችን የሚፈጥር አሠራር በመጠቀም አዲስ አበባ ከምገባው ጎን ለጎን ለልጆቿ ጥራት ያላቸውን አልባሳት በሀገር ውስጥ ዲዛይነሮች በማቅረብ ያለ ጭንቀት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማድረግ የሚያነሳሳ እንደሆነ ተገልጿል።

## ‹‹በቀኝ እጃችን ልማታችንን…

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር አንዱ ትኩረት የተሰጠው አትክልትና ፍራፍሬ መትከል መሆኑን ማሳየት ነው:: ምድራችንን ማደስ፣ የኢትዮጵያውያንን አመለካከት በማደስ ኢትዮጵያን ማደስ አለብን:: በአሮጌ አስተሳሰብና አተያይ ኢትዮጵያን የመሰለ ታላቅ አገር ማስቀጠል ያስቸግራል:: ስለሆነም ሕጎችን፣ አሠራሮችን እያሻሻልን ነው፤ ቤቶች እያደስን ነው፤ የቆሙ ፕሮጀክቶችን በማፋጠን እየተጠናቀቁ ነው፣ ይህ በቂ ስላልሆነ ችግኞችን በመትከል ምድራችን እያደስን ነው ብለዋል::

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ አገራችንን ለማስቀጠል ሰብሰብ ብሎ ከክፉ አስተሳሰቦች ጭንቅላታችን ማደስ አስፈላጊ ነው:: ዕጽዋቶች በተባይ እንዳይጠቁ ኬሚካል እያመነጩ ይከላከላሉ፣ እኛም አርሶ አደሮችን፣ ሴቶችን እና ሕጻናትን በጠራራ ጸሐይ የሚጨፈጭፉ ክፉ ጠላቶችን ከዕፅዋቶች በመማር ራሳችን መከላከል ያስፈልጋል::

ኢትዮጵያን ንፁሓን ዜጎች መኖር የማይችሉባት ምድር ለማድረግና የያዝናቸውን መልካም ሃሳቦች ለማጨናገፍ የሚሞክሩ ኃይሎችና ተላላኪዎቻቸው ትልሞች እንዳይሳካም መከፋፈል ሳይሆን ሰብሰብ ብለን በተደመረ ክንድ ጠላቶቻችንን ማሳፈር ያስፈልጋል ብለዋል::

ዛሬ ከወታደርና ከፖሊስ ጋር በቀጥታ መግጠም የማይችሉ ተላላኪ ባንዳዎች ንፁሓን ኢትዮጵያውያንን ይጨፈጭፋሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፥ ይህን ማስቆም ከሁሉም የሚጠበቅ መሆኑን አጽዕኖት ሰጥተው የተናገሩ ሲሆን ዜጎቻችንን የጨፈጨፉትንም በሕግ አግባብ ማስተማር ይጠበቅብናል ብለዋል::

በቀኝ እጃችን ልማታችንን በማስቀጠል በግራ እጃችን ደግሞ ጠላቶቻችንን በመዋጋት ሀገራችንን ለመለወጥ እንሠራለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት አንድ ሰው መቶ ችግኝ የመትከል መርሐ ግብር እንጀምራለን ሲሉ ገልጸዋል::

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን አረንጓዴ አሻራቸውን ባሳረፉበት ወቅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ዓለምን ያስደመመ ሥራ ተሠርቷል:: ለዚህ ዘመን ትውልድ የሚመጥን በበጎ መልኩ ሊወረሱ የሚችሉ ተግባራትን ማውረስ አለብን:: በዚህ ዘመን ዓለም መተባበርን ማሳየት አለበት ብለዋል::

በዚህ ዘመን የተቀረው ዓለም መደማመጥ፣ መተማመንና መተባበር አለበት:: ኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሩ ኢትዮጵያ ለስነምህዳር መጠበቅ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑ ማሳያ ነው:: ሁሉም ዜጋ በሰላም፣ በአንድነት፣ በመናበብ፣ አንድ በመሆን አገሩን መቀየር መቻል አለበት ብለዋል::

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የ2014 የአረንጓዴ አሻራ በትብብር በአንድነት ሀገርን መለወጥ እንደሚቻል ማሳያ ነው::በአንድነት ሀገርን ማስቀጠል እንደሚቻል ያሳየ ነው:: በየዘመኑ በበጎ የሚወረሱ ጉዳዮች አሉ:: ከሁሉም በላይ ይህ ዓይነቱ ሥራ ትልቅ ትርጉም አለው::

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን በበኩላቸው በመርሐ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ በዘንድሮው ዓመት ከተዘጋጁት 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ችግኞች መካከል 52 በመቶ የሚሆኑት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሲሆኑ 47 በመቶው የደን ችግኞች ናቸው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት 18 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። የጽድቀት መጠናቸውም ከ80 በመቶ በላይ ነው። ችግኞቹ የመሬት መራቆትን በመግታት፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቀነስ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና አላቸው ብለዋል።

ልክ እንደ አረንጓዴ አሻራ በሌሎች ሥራዎቻችንም ሕዝቡን ማስተባበር ቢቻል ሀገርን ማሳደግ ይቻላል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከአገር አልፎ ለአምስት ጎረቤት ሀገራት ማዳረስ መቻሉን ጠቁመዋል:: ከ2000 ዓ.ም ጀምሮም የደን ጭፍጨፋ መጠኑ በ23 በመቶ እየቀነሰ እንደሆነ ተናግረዋል::

ችግኞቹ በ121 ሺ የተለያዩ የችግኝ ጣቢያዎች ውስጥ የተዘጋጁ ሲሆን በዚህም ከ184 ሺ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የስራ እድል መፍጠር እንደተቻለና ከእነዚህ ውስጥ 46 በመቶዎቹ ሴቶች እንደሆኑም ገልጸዋል::

በችግኝ ተከላው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞች በደንብ እየተለዩ እየተተከሉ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ለአብነትም በዘንድሮው የችግኝ ተከላ 500 ሚሊዮን የሚሆነው የአቮካዶ ችግኝ ነው ብለዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ችግሮችን በመንቀልና ችግኞችን በመትከል የኢትዮጵያ ብልጽግና ይረጋገጣል!

ሀገራችን ኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻን ከጀመረች እነሆ አራተኛ ዓመቷን እያስቆጠረች ነው። በነዚህ ዓመታት ራስንና መጪውን ትውልድ ያካተቱ ሀገርን እንደ ሀገር አረንጓዴ የማልበስ ሥራዎች በስፋት ተከናውነዋል። የተገኘውም ውጤትም ዓለም አቀፍ እውቅና ያስገኘ ፤ተጠቃሽ ሀገራዊ ስኬትም ጭምር ነው።

የሰው ልጅ የዛሬውም ሆነ መጪው ዘመኑ ብሩህ እንዲሆን ከሁሉም በላይ ከተፈጥሮ ጋር ያለው መስተጋብር ጤናማ መሆን እንዳለበት ፤ ተፈጥሯዊ የመኖሪያ አካባቢውን/መሬትን የመጠበቅና የመንከባከብ ከፍተኛ ፍጥረታዊ ኃላፊነት እንዳለበትም ብዙዎች ይስማማሉ። ይህ እውነታ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይም "ምድርን ጠብቃት ተንከባከባት "በሚል ግልፅ ቃል ሰፍሮ ይገኛል።

ይህ በሆነበት ሁኔታ የሰው ልጅ ባለፉት ምዕተ ዓመታት የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢውን በከፋ ሁኔታ በማውደም ያደረሰው ምስቅልቅል መዘዙ አሁን ካለው ትውልድ አልፎ ለመጪዎቹ ትውልዶችም ከፍ ያለ የሕልውና/የስጋት ምንጭ እየሆነ ይገኛል።

በተለይም የሰው ልጅ በተፈጥሮ ደኖች ላይ እስከ ዛሬ ያደረሰውና እያደረሰ ያለው ውድመት ከፍተኛ አየር ንብረት ለውጥ በማስከተሉ ፤የእለት ተእለት ኑሮው በብዙ ተግዳሮቶች እንዲፈተንና ለዚህም ከፍ ያለ ዋጋ እንዲከፍል እየተገደደ ነው።

ድርቅ ፣ ጎርፍ ፣ የአካባቢ አየር ሙቀት ፣ የባህሮች ከፍታ መጨመር ፣ ከፍተኛ አውሎ ንፋስ ወዘተ ከችግሩ የተነሳ ዓለምን እየተፈታተኑ ከሚገኙ ክስተቶች ተጠቃሽ ናቸው ። ይህን ዓለም አቀፍ ችግር ለመፍታት የተለያዩ አማራጮች ቢቀመጡም በዋነኛነት የሚጠቀሰው ግን የተፈጥሮ አካባቢን በአረንጓዴ መሸፈን ነው።

ይህ በወጪም ይሁን በውጤታማነቱ ተመራጭ የሆነውን አማራጭ መፍትሔ አረንጓዴ አሻራ በሚል በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግና ስኬት በማስመዝገብ ሀገራችን በዋነኛነት ተጠቃሽ ነች ።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ወደ ስልጣን መምጣት ተከትሎ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የአረንጓዴ አሻራ ለዘመናት የወደመውን የሀገሪቱን የደን ሀብት እንዲያገግም ከማድረግ ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት የሆነው የከባቢ አየር ለውጥ የሚያስከትለውን ተጽእኖ ለመከላከል ወሳኝ አቅም እንደሚሆን ይታመናል።

ላለፉት ሶስት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ ስር በሀገር አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ የችግኝ ተከላ ፕሮግራሞች 18 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። በዚህም አመት 6 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ቢታቀድም 7.6 ቢሊዮን ችግኞች ፈልተው ሊተከሉ ተዘጋጅተዋል።

በአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካባቢን በአረንጓዴ ከማልበስ ባለፈ ፤ለገበያ ተፈላጊ የሆኑ አትክልትና ፍራፍሬዎችን የችግኝ ተከላው አካል አድርጎ እየተሠራ ያለው ሥራም ቢሆን በምግብ ዋስትናና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው ፋይዳ ከፍ ያለ ነው ።

የችግኝ ተከላው በሀገር አቀፍ ደረጃ በምግብ ራስን ለመቻል የምናደርገውን ጥረት ከማገዝ ባለፈ ፤ለአርሶ አደሩ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ በመሆን ኑሮውን በተሻለ መልኩ አሸንፎ እንዲወጣ አቅም ይፈጥርለታል።

ከዚህም ጎን ለጎን የችግኝ ተከላ ፕሮግራሙ የጎረቤት ሃገራትን እንዲያካትት ፣ በዚህም ሀገራቱ ተጨባጭ ተሞክሮ እንዲያገኙም በማሰብ ባለፈው ዓመት ለአምስት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ችግኝ በማቅረብ የተከላ ፕሮግራም እንዲያካሄዱ ተደርጓል።

ይህ ልምድን ከማጋራት ባለፈ ተፈጥሮ አካባቢን በጋራ የመጠበቅና የመንከባከብ ተነሳሽነት ፤ ከኢትዮጵያ አልፎ የጎረቤት ሀገራት ሕዝቦች የከባቢ አየር ለውጥ ተከትሎ የሚከሰቱ ችግሮችን በመቆጣጠር በተሻለ መልኩ የጋራ እጣ ፈንታን የመቅረጽ ተልዕኮ አካል ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥት ይህን ከፍ ያለ ኃላፊነት ወስዶ እየሠራ ያለው ሥራ በትውልዶች መካከል የትብብርና የመልካም ጉርብትና ሐውልት ሆኖ እንደሚቆም ይታመናል።ከዚህም በላይ የሀገራቱ ሕዝቦች እጣ ፈንታ የተንሰላሰለ ስለመሆኑም ተጨባጭ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ይህንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰንደቅ አድርጎ ያቆመንን ሀገራችንን በአረንጓዴ የማልበስ የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ሀገር አቀፍ አራተኛ ዓመት ፕሮግራም ስንጀምር ይህን እውነታ ታሳቢ በማድረግ ፤ለተሻለ ቁርጠኝነት ራሳችንን ማዘጋጀትና ከፍ ያለ ተነሳሽነት መፍጠር ይጠበቅብናል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ልዩ ክትትል የሚሻው የነዳጅ ድጎማ ማስተካከያ ትግበራ!

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ ነዳጅ በአነስተኛ ዋጋ ከሚሸጥባቸው የአፍሪካ አገራት መካከል ተጠቃሽ እንደሆነች ዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ መረጃዎች ያሳያሉ። በ‹‹ስታቲስታ›› የገበያ መረጃ ተቋም (Statista) መረጃ መሠረት ነዳጅ አምራች ከሆኑት አንጎላ፣ ናይጄሪያ እና አልጄሪያ በመቀጠል በአፍሪካ ውስጥ የነዳጅ ምርቶችን በአነስተኛ ዋጋ ለሕዝቧ የምታቀርብ አገር ኢትዮጵያ ናት።

መንግሥት የነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በማኅበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ አቋቁሞ ሲሠራ ቆይቷል። የዚህ ፈንድ ዓላማ በዓለም የነዳጅ ገበያ ዋጋ ላይ በሚከሰተው የዋጋ ጭማሪ ምክንያት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ወጪ በመደጎም የነዳጅ ገበያ ዋጋን ማረጋጋት ነው።

ኢትዮጵያ በ2014 ዓ.ም የበጀት ዓመት ብቻ ሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ለነዳጅ ግዥ ወጪ እንዳደረገችና ዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ በዚሁ ከቀጠለ ደግሞ በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት አምስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር ለነዳጅ ግዥ ልታወጣ እንደምትችል ከኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የአገሪቱን ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚና የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የአገር ውስጥ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋና የዓለም አቀፉን ዋጋ በማጥበብ በኩል ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ከዓለም ገበያ ዋጋ ጋር የተናበበ የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግ ቆይቷል።

በሥራ ላይ የቆየው ድጎማ ለሁሉም ተጠቃሚዎች፣ ማለትም መደጎም ያለባቸውንና የሌለባቸውን አካላት ሳይለይ፣ ሲሠራበት መቆየቱ በግብይቱ ላይ ኢፍትሐዊነትና ብክነት እንዲሰፍን ማድረጉ ይነገራል። የዓለም ነዳጅ ዋጋን ያገናዘበ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ለተጠቃሚው በየወቅቱ ባለመተላለፉም በዋጋ ማረጋጊያ ፈንዱ ላይ ከፍተኛ ዕዳ እንዲከማች ምክንያት ሆኗል። መንግሥት በነዳጅ ዋጋ ላይ የሚያደርገው ድጎማ አገሪቱን ለ132 ቢሊዮን ብር የዕዳ ክምችት እንድትጋለጥ አድርጓታል።

ነዳጁ አገር ውስጥ ከገባ በኋላም ለግብይት የሚቀርበው ከተገዛበት ዋጋ በግማሽ ባነሰ ገንዘብ ነው። ግብይቱም መንግሥት በሚከተለው የድጎማ አሠራር መሠረት እንደ ኬንያ፣ ጅቡቲ፣ ሱዳንና ሶማሊያ ያሉ ጎረቤት አገራት ጋር ሲነፃጸር በግማሽ ያነሰና ሰፊ የዋጋ ልዩነት እንዲኖረው አድርጎታል።

ይህም አገሪቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታስገባው ነዳጅ ወደ ጎረቤት አገራት ኮንትሮባንድ እንዲወጣና በአገር ውስጥ የነዳጅ ሥርጭት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲያሳድር ምክንያት ሆኗል። ነዳጅ አቅራቢ ግለሰቦችና ድርጅቶችም ነዳጁን የዋጋ ጭማሪ ወዳለበት አካባቢ በመውሰድ የኮንትሮባንድ ንግዱ እንዲስፋፋ አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ የነዳጅ ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ ነው። የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ተከትሎ የነዳጅ ፍላጎት ዝቅ በማለቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የነዳጅ ዋጋ ከፍተኛ ቅናሽ አሳይቶ የቆየ ቢሆንም፣ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ዋጋው እየጨመረ መጥቷል። በዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ምክንያት ‹‹መንግሥትም የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል›› በሚል ሰበብ ነዳጅን ደብቆ በማስቀመጥ እጥረት እንዲከሰት የሚያደርጉ አካላትም አሉ።

ይህን መነሻ በማድረግም ከፍተኛ መጠን ያለው የነዳጅ ኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ያለባቸው አካባቢዎች ተለይተው በእነዚህ አካባቢዎች (የደቡብና ምሥራቃዊ የኢትዮጵያ ክፍሎች) የሚገኙ ከተሞች የስርጭት ማስተካከያ ኮታ በማውጣት እንዲጠቀሙ ማድረግ የሚያስችል እርምጃ ተወስዷል። ችግሩን ሙሉ በሙሉ ማስቆም ባይቻልም በተደረገው ድልድል 70 በመቶ የሚሆነውን የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ማስቆም ተችሏል።

ከላይ የተጠቀሱት ቁጥሮችና እውነታዎች የሚያሳዩት ሃቅ ቢኖር፤ የአገሪቱ የነዳጅ ዘርፍ ግብይት ፈጣን፣ የተቀናጀና ጠበቅ ያለ የቁጥጥርና አስተዳደር ሥርዓት ሊበጅለት እንደሚገባ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግም የነዳጅ ድጎማ ማስተካከያ ከቀጣዩ ወር ጀምሮ እንደሚተገበር ተገልጿል።

መንግሥት የነዳጅ ማስተካከያ ድጎማው አነስተኛ ገቢ ባላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን የኑሮ ጫና ለማቃለል ታሳቢ ያደረገ እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናን በማይፈጥር መልኩ እንደሚካሄድ ገልጿል። ማስተካከያውም ልዩነቱን በአንድ ጊዜ ሕዝቡ ላይ በመጫን ሳይሆን ጫናውን ታሳቢ በማድረግ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ተግባራዊ የሚደረግ እንደሆነና ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅትና ግለሰቦችም የሚደረገው ድጎማ እንደሚቀጥል ተነግሯል።

ታዲያ በነዳጅ ግብይት ዘርፍ ለተፈጠሩ ችግሮች አንድ መፍትሄ ይሆናል ተብሎ የታመነበት ይህ የድጎማ ማስተካከያ የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ ከመንግሥትም ሆነ ከኅብረተሰቡ ልዩ ክትትል ያስፈልገዋል። ሕዝቡ ‹‹የነዳጅ ዋጋ ጨመረ›› በሚል ሰበብ አሁን ባለው ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ላይ ተጨማሪ የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ትልቅ ስጋት አድሮበታል።

በተግባር እንደሚታየው የዋጋ ንረት በየጊዜው ማሻቀብ እንጂ ዝቅ ማለት አልሆነለትም። ይህም የኅብረተሰቡን፣ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል፣ ኑሮ እጅግ የከበደ እንዲሆን አድርጎታል። የዋጋ ንረቱ እንኳን ቅናሽ ማሳየት ይቅርና ባለበት መቀጠልም አልቻለም።

አሁን ያለው የዋጋ ንረት ከእስካሁኑ ሁሉ የከፋ ነው፤ ነገ ደግሞ ከዛሬውም የባሰ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። በአንዳንዶቹ ምርቶች ላይ ደግሞ የሚታየው የዋጋ ንረት ደግሞ ጠዋት እና ከሰዓት በኋላ ሰፊ የዋጋ ልዩነት እስከማሳየት የደረሰ ነው። የማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን መረጃዎች የሚሳዩትም የዋጋ ንረቱ እየተባባሰ መሄዱን ነው።

ይህ የነዳጅ ድጎማ ማስተካከያ ደግሞ ተጨማሪ የኑሮ ውድነት እንዳይፈጥር በንቃት መከታተል ያስፈልጋል። ለሸማቹና ለነጋዴው ኅብረተሰብ ስለድጎማ ማስተካከያው ግንዛቤ መፍጠር፣ በሕገ ወጦች ላይ እርምጃ መውሰድ እና የትራንስፖርት ስምሪቱን በቴክኖሎጂ በማስተሳሰር መቆጣጠር ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

የነዳጅ ማስተካከያ ድጎማው ከተተገበረ በኋላ የድጎማ ተጠቃሚ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችም እስከ ስድስት ወራት ድረስ የዋጋ ጭማሪ እንደማያደርጉ በመንግሥት የተቀመጠው አቅጣጫ በትክክል እየተተገበረ ስለመሆኑ ክትትል ሊደረግበት ይገባል።

በሕገ ወጥ የነዳጅ ግብይት ውስጥ ተሳትፎ እያደረጉ የሚገኙ የነዳጅ ማደያዎችና ግለሰቦችን ተጠያቂ ማድረግ ያስፈልጋል። ከሕዝብ የሚሰወር ወንጀልና ወንጀለኛ አይኖርምና ኅብረተሰቡም ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን ሲያስተውል ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ጥቆማ መስጠት ይኖርበታል።

ነዳጅ የማታመርተው ኢትዮጵያ፤ ነዳጅ አምራች ከሆኑ አገራት በላይ ባነሰ ዋጋ ነዳጅ ለዜጎቿ የምታቀርበው መንግሥት ለዘርፉ በሚያደርገው ድጎማ ምክንያት ነው። ድጎማው የነዳጅ ገበያ ዋጋን በማረጋጋት አዎንታዊ ሚና ማበርከቱ ባይካድም በአተገባበሩ ምክንያት አገሪቱን ለእዳ የዳረጉ ችግሮች ተፈጥረዋል።

ለኑሮ ውድነት መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች እንኳንስ የተደራጀ የመረጃና የሰው ኃይል መዋቅር ካለው ከመንግሥት ይቅርና፣ ከግለሰቦችም የተሰወሩ ተዓምራዊ ነገሮች አይደሉም። ነገም በድጎማው ትግበራ ላይ የሚከሰቱት ችግሮችም ሆነ መፍትሄያቸው መንግሥት የማያውቃቸው ሊሆኑ አይችሉም።


በሕገ ወጦች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ ለመውሰድ፣ መዋቅራዊ ማሻሻያ ለማድረግ፣ ከፖለቲካ ሴራ ለመላቀቅ የሚያስችል ቁርጠኞነት እንዲሁም ከራስ ጥቅም ይልቅ ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት የሚያስችል ፍላጎትና ድፍረት ሊኖር ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# ‹‹የሰኔ የጅምላ ግዢን ሙሉ ለሙሉ አስቁመናል››

**-አቶ ሃጂ ኢብሳ**
**የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**



ፎቶ፦ ፀሐይ ንጉሤ

ምሕረት ሞገስ

**ሰኔ ሲመጣ በመንግስት ተቋማት ጎልተው ከሚታዩ ተግባራት መካከል የግዥ ጥድፊያ ዋነኛው ነው። በጀት እንዳይቃጠል በሚል ሰበብ በችኮላ ብዙ ግዥዎች ይፈፀማሉ። በዚህ ሳቢያ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ይጋለጣል። ጊዜው ደረሰ በሚል ሰበብ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ግዥዎች ከመከናወናቸው በተጨማሪ የጥቅም ትስስር የሚካሄድበት ሁኔታ ስለሚፈጠር በተለያየ መልኩ ሙስና ይፈፀማል። ይህንን ችግር ለማቃለል ምን እየተሠራ ነው? ከማለት በተጨማሪ ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን በመያዝ ወደ መንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በማምራት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሃጂ ኢብሳን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።**

**አዲስ ዘመን፡- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እየሠራ ካለው ሥራ እንጀምር፤ ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ሃጂ፡-** የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣን በዚህ ስም የተሰየመው ካለፈው መስከረም ጀምሮ ነው። ሲሰየም ከዚህ በፊት ከነበረው ኃላፊነት በተጨማሪ ሌሎች ኃላፊነቶችም ተሰጥተውታል። ተጠሪነቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሲሆን፤ የግድ በዛ መስመር የሚያልፉ ነገሮች ይኖራሉ። አምና ከሃምሌ እስከ መስከረም በወቅቱ ለነበሩት 191 የፌዴራል ተቋማት ሙሉ ስልጠና ስንሰጥ ነበር። በሶስቱ ወራት በአጠቃላይ ግዥ ፣ በመንግስት የኤሌክትሮኒክስ ግዥ፣ በንብረት አያያዝ፣ በኦዲት እና በሌሎችም በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ሥልጠና ሰጥተናል። ከስልጠና በኋላ ደግሞ በግላችን ስልጠናው ምን ለውጥ አምጥቷል? በሚል የዳሰሳ ጥናት አካሂደናል።

ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ደግሞ ሞዴል ዩኒቨርሲቲዎችን ለመፍጠር በተለየ መንገድ (ሲናሪዮ) ስልጠና ጀምረናል። የዩኒቨርሲቲ ግዥ ንፁህ እንዲሆን ፤ ሙሉ ለሙሉ ንፁህ እንኳን ባይሆን አነስተኛ ክፍተት ብቻ እንዲኖርበት ለማድረግ ጠንካራ ሥራ አከናውነናል። ከ47ቱ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ከ43ቱ ጋር ደብረዘይት ላይ ውይይት አድርገናል። ፎረም በማበጀት በስድስተኛው ወር ላይ ቦንጋ ላይ አካሂደናል። ዩኒቨርሲቲዎችን በሶስት የከፈልን ሲሆን፤ በግዥ ላይ፣ በመንግስት ሃብት እና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተሉትን እና ትልቅ ክፍተት ያለባቸውን ‹‹ቀይ›› ብለን ለይተናል።

ጥቃቅን ስህተት ያለባቸውን ‹‹ቢጫ›› ያልን ሲሆን፤ በርካታ ክፍተት የሌለበት እና ወደ ንፁህ የሚጠጋውን ‹‹አረንጓዴ›› ብለን ዩኒቨርሲቲዎቹን ሶስት ቦታ ከፍለናል። የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች ባሉበት 43ቱ ዩኒቨርሲቲ ከእያንዳንዱ ሁለት ሁለት ከፕሬዚዳንት እና ከፋይናንስ ዘርፍ ከሚመለከተው ጋር ውይይት አድርገናል። ስለዚህ ባለፈው ስልጠና መሠረት ከአንድ ተቋም በስተቀር ሁሉም የፌዴራል ተቋማት የግዥ ዕቅዳቸውን እንዲያቀርቡ አድርገናል። በ2014 በዕቅዳቸው መሠረት መስራታቸውን እያየን ነው። በ2014 የተሻለ ክትትል አድርገናል ማለት ይቻላል። ነገር ግን በርካታ የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉ ማየት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ 2014 ላይ ፈተና አላጋጠማችሁም?**

**አቶ ሃጂ፡-** አጋጥሞናል። አንደኛው ተግዳሮት ልዩ ፍቃድ ነበር። ከጥቅምት ጀምሮ በነበረው ጦርነት ምክንያት ልዩ ፍቃድ ይበዛል። ለምሳሌ መከላከያ የሚገዛቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ። እነዛ ሁሉ ግዥያቸው የሚከናወነው በልዩ ፍቃድ ነው። የአገር ጉዳይ እና ጦርነት በመሆኑ ወደ ጨረታ መሔድ አይቻልም። ከዛ ውጪ ለምሳሌ በሰሜኑ አካባቢ ቁስለኞችን ሰብስበው የሚያክሙ ፣ የሚያበሉ እና የሚያጠጡ በርካታ ሆስፒታሎች ልዩ ፍቃድ ተሰጥቷቸዋል። እዛ ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባም ጦር ሃይሎች እና የመከላከያ መምሪያም ልዩ ፍቃድ ነበራቸው።

ጦርነቱም ትንሽ መለስ ካለ በኋላ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ ለሙሉ ውድመት አጋጥሟቸው ነበር። ለምሳሌ ወልዲያ እና ወሎ ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ ለሙሉ ወድመው ነበር። ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ካምፕ ሆኖ ነበር። ፍራሽ፣ ወንበር፣ በርና ሌሎችም መጠቀሚያዎች ተሰባብረው ነበር። ወያኔ ደብረሲና ሲደርስ ካምፕ ለሠፈሩት የሠራዊቱ አባላት ምግብ መቻል የግድ ያስፈልግ ነበር። ይህ ትልቅ ፈተና ነበር። ለፌዴራል ፖሊስም ሙሉ ለሙሉ ልዩ ፍቃድ ሲሰጥ ነበር። ካቀድነው የተለየብን ይህ ነው።

ተቋማት በዕቅዳቸው መሠረት እንዲሠሩ አቅደን ነበር። በእርግጥ በግዥ ህግም ልዩ ፈቃድ ተቀምጧል። ነገር ግን በህጉም ልዩ ፍቃድ ተብሎ የወጣው ከአቅም በላይ ሲያጋጥም ፍቃድ ለማግኘት ነው። በዚህ ምክንያት ተለዋዋጭ ነገር አጋጥሟል። በበርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ጉድለት ታይቷል። ኦዲትም የማናደርጋቸው ዩኒቨርሲቲዎችም አጋጥመዋል። ለምሳሌ ቡሌሆራ ላይ በኦሮሚያ ካለው የሸኔ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ኦዲት ማድረግም ሆነ መቆጣጠር እና መከታተል አይቻልም። አማራ ክልል ላይ ከላይ የጠቀስኳቸውን ዩኒቨርሲቲዎች ጨምሮ ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ እና አራት አምስት ዩኒቨርሲቲዎች ከአቅም በላይ ችግር ያጋጠማቸው አሉ።

ሰላማዊ አካባቢ የተባለው ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ራሱ ካምፕ ሆኖ ስለነበር እና ቁስለኛ ያስተናግዱ ስለነበር በግዥ ህጉ እንዳንሔድ ወደ ልዩ ፍቃድ የምንሔድበት አግባብ ላይ ደርሰናል። ይህ ማለት እኛ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የምንፈልገው ግዥ የጨረታ ነው። ጨረታ ሁሉም የንግዱ ማህበረሰብ የሚወዳደርበት ነው። ከውድድር ደግሞ መንግስት ትርፍ ያገኛል። ሃያ ሰላሳ ተወዳዳሪዎች ቢኖሩ እና በቴክኒክ የተወሰኑት አልፈው በፋይናንስ ሲወዳደሩ ዝቅተኛ ያቀረበው ያሸንፋል። በዛ ትርፍ መንግስት ይጠቀማል።

ያለ ጨረታ ግዥ ሲፈቀድ አንደኛ የመልካም አስተዳደር ችግር ይፈጠራል። ሁለተኛ ልዩ ፍቃዱ በመሰጠቱ የማቅረብ ዕድሉን ለአንዱ ሲሰጥ ጎረቤትየው ለኔ ለምን አልተሰጠም? ይላል። ለምሳሌ ተቋሙ ‹‹ከአንዱ ካምፓኒ ለሠራዊቱ ጫማ እገዛለሁ›› ካለ አትግዛ ተብሎ አይከለከልም። ይፈቃዳል። ሌላ ካምፓኒ ደግሞ ለምን ከኔ ጫማ አልተገዛም? ብሎ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል። ስለዚህ እንደዚህ አይነት ነገር ተግዳሮት ሆኖብናል። ባሰብነው ልክ በዕቅድ ለመሔድ አዳግቶናል። ይሔ በፌዴራል ተቋማትም ሆነ በዩኒቨርሲቲዎች አጋጥሞናል።

**አዲስ ዘመን፡- ሌላስ ያጋጠማችሁ ችግር ምን ነበር?**

**አቶ ሃጂ፡-** እኛ የምንሠራው ሌላም አለ። ኦዲት ሥራ ላይ አንዱ የገጠመን ችግር ብዙ ጥቆማዎች ይመጣሉ። በዚህ ተቋም ላይ ሙስና አለ። ሌብነት አለ ይባላል። በማወቅ፣ በመተዋወቅ፣ በወዳጅነት እየሠሩ ነው ይባላል። ጥቆማውን ተከትሎ ግዥውን በማስቆም ኦዲት ይደረጋል። ኦዲት ሲደረግ ጥቆማው ትክክል ከሆነ ግዥው ይሠረዛል። የተጠቆመው ጥቆማ ደግሞ ስህተት ከሆነ ግዥው እንዲቀጥል ይደረጋል።

በተጨማሪ አቤቱታ እና ጥፋተኝነት የሚል ዳይሬክቶሬት አለ። ይህ ክፍል የከፊል ዳኝነት ሥራን ይሠራል። በእዚህ ውስጥ ከ70 በመቶ በላይ ተቀጣሪዎቹ ህግ የተማሩ ዳኞች ናቸው። የፍትሓ ብሔርም ሆነ የወንጀል ህጎችን አጣቅሰው ውሳኔ ያስተላልፋሉ። አቅራቢ እና ተቀባይ ሁለት ተቋማት ይካሰሳሉ። ማንኛውም የፌዴራል ተቋምም ሆነ አቅራቢ ይከሳል፤ በሌላ በኩል ሌላኛው ደግሞ ይከሳል። በሚካሰሱበት ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ሳይሆን ወደ እኛ ይመጣሉ። እንደማንኛውም የፍርድ ቤት መስመር ህግን ተከትለን መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን ይዘን እንመረምራለን።

በገንዘብ ሚኒስቴር የሚመራ አምስት አባል ያለው ቦርድ አለ። ከምርመራው በኋላ ለእርሱ ይቀርብና ቦርዱ አይቶ ወሳኔ ያሳልፋል። ውሳኔ እኛ ካሳለፍን በኋላ ውሳኔው ትክክል አይደለም ብሎ የሚቀጥል አካል ካለ ወደ ፍርድ ቤት ይቀጥላል። ፍርድ ቤት ድረስ እስከ ሰበር መቀጠል ይችላል። ለምሳሌ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጉዳይ መጀመሪያ ቦርዱ ለዩኒቨርስቲ ወሰነ፤ አቅራቢው ትክክል አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ሔደ። ፍርድ ቤት ደግሞ ለአቅራቢው ወሰነ፤ እያለ ቀጠለ፤ መጨረሻ ላይ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ቦርዱ የወሰነውን አፀና፤ ዩኒቨርሲቲው አሸነፈ። ስለዚህ የምንሰራው ከፊል ዳኝነት ነው።

ከዛ ውጪ አስቸግሮን የቆየው ጨረታ ላይ ዋጋ ሰብሮ መግባት ነው። ለምሳሌ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ላይ የእንጀራ ገበያ ሽያጭን በሚመለከት በ6 ብር የሆነውን በ4 ብር አቀርባለሁ ብሎ ያሸንፋል፤ ይገባል። ሁለት ጊዜ አቅርቦ ዋጋ አስተካክሉ ይላል። ከዛ ወደ ጭቅጭቅ ይገባል። በሌሎች ሥራዎች ላይም ዋጋ ሰብሮ መግባት ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ነው። ቴክኒክን ያልፉሉ፤ ዋጋ ሰብረው ገብተው ሥራውን አያጠናቅቁም። ከአራት ከአምስት ወር በኋላ ብረት ጨምሯል፤ ሚስማር ጨምሯል ብለው ይጨቃጨቃሉ።

> **ት**ክክለኛውን ዋጋ ያቀረበው ሰው የመውደቅ ዕድል ያጋጥመዋል።

ትክክለኛውን ዋጋ ያቀረበው ሰው የመውደቅ ዕድል ያጋጥመዋል። ትምህርት ቤትም ሆነ የጤና ተቋማት እንዲሁም ማንኛውም የሚገነባው ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ ዋጋ ሠብሮ ገብቶ ፤ ሌላ ክስ እና ጭቅጭቅ ውስጥ ከመግባት ፤ ባሻገር ፕሮጀክቱ ይዘገያል። የሁለት ዓመቱ ፕሮጀክት አራት ዓመት ይፈጃል። የአራት ዓመቱ ፕሮጀክት ስምንት ዓመት ሲፈጅ ሌላ ተጨማሪ ወጪ ያስከትላል፤ መንግስትንም ይጎዳል።

ገንዘብ ሚኒስቴር ሆኜ በተደረገው ጥናት የመንግስት ፕሮጀክቶች ከአምስት እስከ አስር ዓመት በመዘግየታቸው ምክንያት እስከ 43 ቢሊዮን ብር መንግስት ለተጨማሪ ወጪ ይጋለጣል። በወቅቱ ቢጠናቀቁ ግን ይህ 43 ቢሊዮን ብር ለሌላ የልማት ተግባር ይውል ነበር። ስለዚህ ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ክፍተት የሚፈጠረው አንድም በደንብ አይጠናም፤ በደንብ ሳይጠና በትዕዛዝ ይጀመራል። ዋጋ ሰብሮ መግባት ታክሎበት መሃል ላይ ሲደርስ ፕሮጀክቱ ይቆማል።

በተጨማሪ ለዛ ፕሮጀክት የሚበቃ በጀት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር የፕሮጀክት ጥናት ይጠናል። በፕላን ሚኒስቴር በኩል ለፓርላማ ቀርቦ ፓርላማ ላይ ከፀደቀ በኋላ፤ እያንዳንዱ አዲስ የፀደቀው ፕሮጀክት በጀት መኖሩ ተረጋግጦለት መቼ እንደሚጀምር፣ ማን እንደሚሠራ፣ ይህንን ሥራ ላይ ያላዋለ የመንግስት አካልም ይሁን ሌላ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

በህግ እንደሚቀጣ ተለይቶ መግባባት ላይ አይደረስም፤ ስለዚህ ፕሮጀክት ይዘገያል።

**አዲስ ዘመን፡- እዚህ ላይ የአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን የዓለም የገበያ ሁኔታ ራሱ በፍጥነት እየተለዋወጠ ከመሆኑ አንፃር ፕሮጀክቶች ቀድሞ ከተያዘላቸው ገንዘብ በላይ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲፈጠር ይችላል? እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሃጂ፡-** ልክ ነው፤ ሁሉ ነገር ተገለባብጧል። ትናንት የነበረ ዛሬ የለም። ከዓመት በፊት ውል የገባ ኮንትራክተር ዛሬ በዛ ጊዜ ዋጋ ጨርስ ማለት ያስቸግራል።

**አዲስ ዘመን፡- አዎ! ይህንን ጉዳይ እንዴት እያስተካከላችሁት ነው?**

**አቶ ሃጂ፡-** ሁሉም ነገር ጥቅም እና ጉዳት አለው። አሁን ለምሳሌ ከዚህ በፊት በነበረው ልማድ የአፍሪካ እና የዓለም ዋጋ በተረጋጋበት ሰዓት ውል ይታደሳል፤ የሚል ነገር አልነበረም። ምክንያቱም ሽርክና የሚፈጠርበት ሁኔታ ይኖራል በማለት ፕሮጀክቱ አምስት ዓመት ይፈጃል ከተባለ አቅራቢው ወይም ገንቢው በአምስት ዓመት ውስጥ የምጨርስበትን ሁኔታ እፈጥራለሁ ይላል። አሁን ግን ውሉ እንደአስፈላጊነቱ የሚታደስበት ሁኔታ እናስገባለን። በተለይ የዓለም ገበያ እስከሚረጋጋ ድረስ ይህን መከተል የግድ ነው። ምክንያቱም ሲሚንቶ ከአንድ ዓመት በፊት አራት መቶ እና አምስት መቶ ብር ነበር። አሁን ግን ስምንት መቶ እና አንድ ሺህ ብር ገብቷል። ስለዚህ ሲሚንቶ አራት መቶ ብር በሆነበት ጊዜ ኮንትራት የወሰደ ሰው ሲሚንቶ አንድ ሺህ ሆኖበት በዚህ ጨርስ ማለት ጫና መፍጠር ነው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በዚህች ቀዳዳም አላግባብ መንግስት እንዳይጎዳ ማሰብ የግድ ነው።

መንግስት ከህዝብ ያገኛትን ትንሿን ገንዘብ ይዞ የሚያስተዳድር በመሆኑ በጣም በጥንቃቄ መሠራት እንዳለበት ሊረሳ አይገባም። ውሉ ይሻሻላል ተብሎ ቢቀመጥም፤ ምን ሲሆን ይሻሻላል? የሚለው በጥንቃቄ በግልፅ መቀመጥ አለበት። በቅርቡ ገንዘብ ሚኒስቴር ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በተለይ ነባር ፕሮጀክቶች ውላቸው በወቅታዊ ዋጋ እንዲስተካከል እና ገበያውንም ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባጠናው መሠረት እንዲስተካከል የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው። በሌላ በኩል ዩኒቨርስቲዎች ላይ የተማሪ ቀለብ ላይ ጤፍ ሶስት ሺህ በነበረበት ጊዜ ኮንትራቱን የወሰደ አካል አሁንም በዛው ዋጋ አቅርብ ማለት አይቻልም። ስለዚህ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ በሚያጠናው መሠረት አስተካክሉ እያልን ነው። ምክንያቱም ዩኒቨርስቲዎች ተማሪ ይዘው መሰቃየት ስለሌለባቸው ውሉ ላይ ባይኖርም በፍጥነት ከማዕከላዊ ስታትስቲክስ ጋር እየሰሩ ወዲያው እኛን እያሳወቁ በጋራ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው።


ለእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ እና ለእያንዳንዱ ተቋማት ሳይሆን ተመሳሳይ አካባቢዎች በምስራቅ ፣ በምዕራብ እና በሌሎችም አካባቢዎች ያለውን ዋጋ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ በ27 ቅርንጫፎቹ እያጠና ዋጋውን ይገልፃል። በዛ መሠረት ማሻሻያ ያደርጋሉ። በተለይ ለተማሪዎች በዚህ መልኩ የምግብ ዋጋ እየተስተካከለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሌላ ከስልጠናው ባሻገር የምትሠሩት ምንድን ነው? የሰኔ ግዥን በሚመለከትስ ምን ይላሉ?**

**አቶ ሃጂ፡-** አሁንም ስልጠና መስጠታችንን እንቀጥላለን። አምና ስንሰራ እንደከፍተት ያየነው አንድ ተቋም ያምጣ እንጂ የሚፈፅሙት ግዥዎች በዕቅድ ውስጥ የተካተቱ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው አይታይም ነበር። የሰው ሃይልም አልነበረም። አሁን ግን እንከታተላለን። አንድ ተቋም ዕቅድ ሲያመጣ ለመግዛት ያሰበው ምንድን ነው? የሚገዛው መቼ ነው? የሚለውን እንከታተላለን። ይህንን ያደረግነው የሰኔ ላይ ግዥን ሙሉ ለሙሉ ለመከላከል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድም ከግንቦት ጀምሮ ግዥ ይቁም ብለዋል። እኛም ሚያዚያ ላይ ልዩ ፍቃድ እና ልዩ ግዥ የሚባል ሙሉ ለሙሉ እንዲቆም አቅጣጫ አስቀምጠናል። ገንዘብ ሚኒስቴርም ግዥ እንዲቆም ብሏል። ነገር ግን አሁንም ልዩ ፍቃዱ ቀጥሏል። አንዳንዴ ግን ቢከለከልም የሚያሳምን ፈቃድ የሚያስፈልገው ያጋጥማል። ለምሳሌ የወረርሽኝ በሽታ ቢያጋጥም አንዴ ግዥ ከልክያለሁ እና አልፈቅድም ማለት አይቻልም። በእርግጥ ትንንሽ ግዥዎች እስከ ሰኔ 30ም ሊያጋጥሙ ይችላሉ።

አንድ ሃላፊ ጉዞ እየሔደ ጎማው ቢበር አይገዛም ለማለት ይከብዳል። ነገር ግን ሰኔ ላይ በጅምላ እና በብዛት ግዢዎችን ማካሔድ አይቻልም። በዚህ ዓመት



**20 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንከን የለሽ ግዥ መፈፀም ከቻሉ፤ ዩኒቨርሲቲዎችም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የጠራ ግዥን ከፈፀሙ 50 በመቶ የአገሪቷ ግዥ የተጣራ ይሆናል። ነገር ግን ይህንን በአንድ ጊዜ ማምጣት አይቻልም**

የምንሠራው የተለየ ሥራ እያንዳንዱ ተቋም አቅዶ ከመጣ በኋላ ለዕቅዱ ምላሽ መስጠት፤ ተቋማቱ ለግዥ እኛን የሚጠይቁን ነገሮች በሙሉ በዕቅድ ውስጥ የተካተተ መሆኑን እናያለን። ብዙ ተቋማት ትኩረት አይሰጡም። የአምናውን ወይም የካቻምናውን ገልብጠው ያመጣሉ። እኛም አይተን አንተችም፤ እንዲሁ እናስቀምጣለን። ተቋማቱም ዕቅዳቸው ውስጥ የሌለ ግዥን ይጠይቃሉ። ተከታትሎ የሚያመሳክር አልነበረም። አሁን ግን ፋይሉን አስወጥተን እንጠይቃለን።

ግዥ በጣም አድካሚ ሥራ ነው። አንደኛ የውስጥ ድክመት አለ። የግዥ ሥርዓቱ ላይ በተለያየ መልኩ የተለመዱ ነገሮች አሉ። እነዛን ልማዶች በአንድ ጊዜ ጠራርጎ ማጥፋት አይቻልም። ሽርክና ይኖራል። ለምሳሌ የጨረታ ግዢ አራት ወር ይፈጃል። ስለዚህ ለአስቸኳይ ጉዳዮች የለቀማ ግዢ እና ውስን ግዢ ይፈቀዳል። በዛ ጊዜ አምስት አቅራቢ ቢወዳደር እነማን እንደሆኑ የሚያውቀው አንድ አምላክ ነው። መቀራረብ እና አብሮ መስራት ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ የመንግስት ተቋማትን ግዥ ለመቆጣጠርና የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከታተል የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ አቅም ምን ያህል ነው?**

**አቶ ሃጂ፡-** ሙሉ በሙሉ የመንግስት ተቋማትን ግዥ ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም አለን አልልም። የሰው ሃይል ብዛት ሳይሆን ጥራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ አጠቃላይ የአገሪቷን የግዥ ሥርዓት የሚመራ የግዥ ዳይሬክቶሬት አለ። ይህንን የግዥ ሥርዓት የሚመራ ሰው በዕውቀትም ሆነ በልምድ ትልቅ ዓቅም ያለው ጠንካራ ሰው መሆን አለበት። እንደዚህ ዓይነት ሰው ለመያዝ ደግሞ ደመወዝ ይፈልጋል። ጥራት ያለው የሰው ሃይል ለማግኘት ጥራት ያለው ክፍያ ይፈልጋል።

የውስጥ ግዥ ዳይሬክተር እና የአጠቃላይ ግዥ ዳይሬክተር ደመወዛቸው አንድ ዓይነት ነው። ከገበያ የማገኘው ከማንኛውም የግዥ ዳይሬክተር የበለጠ አቅም ያለው መቅጠር አይቻልም። ይህንን ለማስተካከል ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በደንብ ተነጋግረናል። በደመወዝም በጥቅማጥቅምም ሆነ በሥራ ልምድ የበለጠ መሆን እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል። የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንትን ለማነጋገር የሚመጥን ላፊ መኖር አለበት፤ ተባብለን ተነጋግረናል።

አቤቱታ እና ማጣራትም በተመሳሳይ መልኩ ዳኝነት ነው። የዳኞች ደመወዝ የተሻለ ነው። ስለዚህ ከእኛ እየለቀቁ ወደ እዛ ይገባሉ። ምክንያቱም የቤት አበልን ጨምሮ ብዙ የደመወዝም ሆነ የሌሎች ጥቅማጥቅሞች ልዩነት ያለበት በመሆኑ ከእኛ ለቅቀው ወደ እዛ ይገባሉ። ከእኛ ለቅቀው አምስት እና ስድስት የሚሆኑ የህግ ባለሞያዎች ዳኛ ሆነዋል። ኦዲትም በተመሳሳይ መልኩ ሌላ ቦታ የተሻለ ደሞዝ ሲያገኙ ይለቃሉ። ስለዚህ በተለይ ሶስቱ ዋና ዋናዎቹ ላይ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር ተስማምተናል። ነገር ግን ፀድቆ አልመጣልንም ይፀድቃል ብለን እናስባለን። ስለዚህ ትንሽ የተሻለ ክፍያ ፈፅመን የተሻለ ሥራ የምንሠራበት ሁኔታ ይኖራል። በ2015 የተሻለ ነገር እንጠብቃለን።

**አዲስ ዘመን፡- ባለፈው ዓመት አሠልጥነናል ብላችኋል። ስልጠናዎችን ሰጥታችሁ በትክክል ውጤት መምጣቱን ትከታተላላችሁ?**

**አቶ ሃጂ፡-** ስልጠና ከባድ ነው። ስልጠና አልጋ ላይ ተኝቶ አበል ወስዶ መምጣት አይደለም። አሰልጥኖ አብቅቶ ውጤት ማምጣት መቻል የግድ ነው። በምንፈልገው ደረጃ ላይ አልደረስንም። ለዳይሬክተር ለተዘጋጀው ስልጠና ተቋማት ጀማሪ ባለሙያ ይልካሉ። ቡድን መሪ ተጠርቶ ጥበቃ ይልካሉ። የግዥ ባለሙያ እየተባለ የአይ ቲ ባለሙያ ይልካሉ።

ካለፈው ዓመት ስልጠና ምን ተገኘ? ከተባለ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ከባድ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። በመገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ቀርቦ ሲተች ነበር። በኋላ ይሔንን ተከታትለን የእኛን ኦዲተር ልከን ስናጣራ ነገሩ በሙሉ የተበላሸ ነበር። የፋይናንሱን ዘርፍ የሚመራ ምክትል ፕሬዚዳንት ልዩ ፍቃድ የሚሰጥ እርሱ ነበር። ዋጋ የሚያስተካክል እርሱ ነው። ሁሉን ከማድረግ ባሻገር እርሱ ከሌለ እርሱን ተክታ የምትሠራው ፀሃፊው ነበረች። ‹‹ዩኒቨርስቲው አደጋ ላይ ነው›› ብለን ቀይ ከሰጠነው በኋላ ለዩኒቨርስቲዎች በሙሉ ስልጠና ተሰጠ። የግዥ ዳይሬክተር የተቋቋመው ለግዥ ነው። ጨረታ ማውጣት ያለበት ማን ነው? ይህ ሁሉ ሥራ ሲሰራ ፋይናንሱ፣ ኦዲቱ፣ የስነምግባር ክፍሉ ሁሉም ምን እየሠራ ነበር? ብለን ፕሬዚዳንቱም ማየት እንደነበረበት ታምኖ ግለሰቡ ከቦታው እንዲነሳ ተደረገ። በቀላሉ በዛ ዩኒቨርሲቲ ለውጥ አምጥተናል።

**አዲስ ዘመን፡- ያልተገባ ግዥ ሲያጋጥም ምን ታደርጋላችሁ?**

**አቶ ሃጂ፡-** እኛ እኮ ዳኛ አይደለንም። የከፊል ዳኝነት ሥራንም የምንሠራው ተቋማት እና አቅራቢ ሲካሰሱ ብቻ ነው። ኦዲት አድርገን ከሙስና ጋር የተያያዘ ግኝት ካጋጠመ ሰነዱን ለመርማሪ ፖሊስ በመስጠት ሃፊነታችንን እንወጣለን። መርማሪ ፖሊሱ ክብደቱን አይቶ ራሱ ምርመራ አካሂዶ ፍርድ ቤት ይሔዳል። ፍርድ ቤት ደግሞ በራሱ ሲቀጥል እኛን እንደምስክር ወስዶ ውሳኔውን ያሳልፋል። ለዩኒቨርሲቲዎች ትምህርት ሚኒስቴር እርምጃ ይወስዳል፤ እኛ በጀት ከመከልከል ውጪ ምንም ማድረግ አንችልም። ለምሳሌ ጥፋት ላለበት ዩኒቨርሲቲ ማስተካከል ያለብህን ካላስተካከልክ ለአንድ ወር በጀት አንሰጥም እንላለን። ምክንያቱም ከድሃ ጉሮሮ በተሰበሰበ ገንዘብ እንደፈለጉ ማድረግ አይቻልም። ከዛ በኋላ ወዲያው ማስተካከል ያለበትን ያስተካክላል።

የተሳሳተ ጨረታ ወጣ ተብሎ ጥቆማ ከመጣ፤ እናስቆማለን። ነገር ግን የሚወጣውን ጨረታ በሙሉ መቆጣጠር አንችልም። በአንድ ተቋም ተቆጣጥሮም አይቻልም። በየተቋሙ ያሉ የመንግስት ሃላፊዎች ግዴታውን መወጣት አለበት። የእያንዳንዱ ተቋም ሃላፊ የህዝብን ገንዘብ በጥንቃቄ ከጨረታ ጀምሮ እስከ ውስን ግዢ ሃላፊነት በተሞላበት መልኩ መካሔዱን ማረጋገጥ አለበት። አንዳንዴ እኛ ጋር ጥቆማ መጥቶ ኃላፊዎች የማይሰሙበት ሁኔታ አለ።

**20 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንከን የለሽ ግዥ መፈፀም ከቻሉ፤ ዩኒቨርሲቲዎችም ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የጠራ ግዥን ከፈፀሙ 50 በመቶ የአገሪቷ ግዥ የተጣራ ይሆናል። ነገር ግን ይህንን በአንድ ጊዜ ማምጣት አይቻልም።** በፍፁም አልሠርቅም የሚል ዜጋ መፈጠር አለበት። በ2015/በ2014 ያልተሳካውን እናሳካለን ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- በኦዲት ግኝታችሁ መሠረት ምርመራ ተካሂዶ ክስ እንዲመሠረት የመራችኋቸው ጉዳዮች ፍርድ ቤት ቀርበው ውሳኔ ይተላለፍላቸዋል ወይስ እንዴት ነው? ቀይ ነው ብላችሁ እንዳለፋችኋቸው ይቀራሉ ወይስ ምን ታደርጋላችሁ?**

**አቶ ሃጂ፡-** ቀይ ያልናቸው፤ ቀይ እንደሆኑ እንዲቀጥሉ አንፈልግም። ለምሳሌ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ላይ ያጋጠመንን ችግር ለማቃለል ሰውየው ከኃላፊነት እንዲነሳ ማድረግ ተቻለ። እርሱን የተካው ሰው ተመሳሳይ ሥራ እንዳይሠራ እየተከታተልን ሌሎቹንም ሠራተኞች ለማብቃት ጥረት አድርገናል። ሌላው የፍርድ ቤት ሒደት ይታወቃል። አንድ ጉዳይን ወደ ፍርድ ቤት ለማድረስ አራት እና አምስት ወራትን ሊፈጅ ይችላል። መርማሪው ፖሊስ ራሱ ለመመርመር ጊዜ ይወስዳል። በዛ ላይ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ሰፋፊ ወንጀሎች አሉ። ስራ ሊበዛ ይችላል። ሌሎችም ወንጀሎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ስለዚህ ወዲያው በአንድ ዓመት ይሔ ተሰራልኝ ለማለት አንችልም። ነገር ግን በስምምነት እየሰራን ነው።

አዲስ ዘመን፡- ጥቆማ ትቀበላላችሁ? ጥቆማ ከተቀበላችሁ በኋላስ ምን ያህል ትሠሩበታላችሁ?

አቶ ሃጂ፡- በዚህ ዓመት ከሃምሳ በላይ ጥቆማ ተቀብለናል። ሁሉንም አጣርተን ከሃያ በመቶ በላይ ሙሉ ለሙሉ እንዲቆሙ አድርገናል። ዋናው ወደ ከፋ ወንጀል እንዳይሔዱ እናደርጋለን። ነገር ግን በጥቆማ መሠረት ጨረታ እንዲስተካከል ወይም እንዲሠረዝ የምናደርጋቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ካላስተካከለ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንወስዳለን። አሁን ለምሳሌ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስሲቲ ላይ በርካታ ጥቆማዎች ይቀርባሉ። ጉዳዮችን እያየን እየፈታን እንሔዳለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ አመሠግናለሁ።**

**አቶ ሃጂ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

**የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።**

# የሀገራዊ ፖለቲካችን ጉዞ በትራፊክ ምልክቶች ንጽጽር

**መራር ቀዳሚ ትዝብት**

የሀገሬ ፖለቲካ መጨረሻው በማይታወቅ የጭለማ ዋሻ ውስጥ እንዲራመድ እንደተፈረደበት መንገደኛ ለምን “ከዘመን ዘመን” እየተደነቃቀፈ የእውር ድንብር ጉዞ ሲጓዝ እንደሚኖር አልገባኝም፤ ገብቶኝም አያውቅም። መነጋገር ብርቃችን፣ መደማመጥ ቃራችን፣ መከባበር እርግማናችን፣ መቀባበል እርማችን ለምን እንደሆነም መረር ብለን ስንጠይቅ ብንባጅም ዛሬም ምላሽ አላገኘንም።

ይህን መሰሉን ጥያቄ ጠይቀው መልሱን ሳያገኙ ላለፉት ብዙኃን ወገኖቻችንም ማዘኑ ትርጉም የለውም። ለምን ቢሉ የፖለቲካ ቡድኖችን ጉዳይ በተመለከተ እኛ “ቋሚ” ተብዬዎች ከእነርሱ የምንሻለው “ስለምንተነፍስ” ካልሆነ በስተቀር ተስፋችንማ ከሟቾቹ ጋር አሽልቦ ከመቃብር ከዋለ ሰነባብቷል።

ስመ ፖለቲካ በተጠራ ቁጥር ፈጥኖ ወደ አእምሯችን ከተፍ የሚለው መጠላለፍ፣ መጠላላት፣ መገፋፋት፣ ሲጠናም መጠፋፋት ሆኖ እንደ ባህል ተጎናጽፈነዋል። ሕጻናት ልጆቻችን “ምን እንቁላል ድፍን ያየኸን/ያየሽን እንደሆን ...ዐይንህን/ሽን ድፍን” እያሉ እንደሚጫወቱት የልጅነት ዕድሜያቸው መዘናኛ፤ የፖለቲካ ቡድኖች የታቀፉትን “የራእይ እንቁላል” ትእግስትና ማስተዋል ተጎናጽፈው “በመፈልፈል” ለፍሬ እንደማብቃት ለምንና እንዴት መክነውና “ጭር በለው” ምክንያቱ በአግባቡ ሳይገለጥልን ለጉልምስና፣ ለሽበትም ይሁን ለመቃብር የምንበቃው ግራ እንደተጋባን ነው።

ገና ከጽንስ ሳይወጡ “በሽኩቻ ሾተላይ” የመከኑ፣ ከተፈጠሩም በኋላ ለዳዴ ወግ ሳይበቁ “በጥላ ወጊ” የሥልጣን ደዌ እየተጠቁ በአጭሩ ሲቀጩ የኖሩትና ዛሬም እየተቀጩ ያሉ የፖለቲካ ቡድኖችን ማሰቡ በራሱ በሀገራዊ ተስፋችን ላይ በረዶ የመቸለስ ያህል ክፉ ስራይ ሆኖብናል። ይብልጥ ሀዘናችንን የሚያከብደው ደግሞ የሌሎች ሀገራትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕድሜ ማስላትና “እንዴት እንደተከበሩ ኖሩ!?” በማለት ማሰላሰል ስንጀምር ነው።

ለምሳሌ፡- እ.ኤ.አ በ1828 የተፈጠረው የአሜሪካኖቹ የብሔራዊ ሪፐብሊካን ፓርቲ እና በዚያው ዓመት ባለመግባባት ተስማምተው በመለያየት “የታጋሽነት ምሳሌ የሆነችውን አህያ” የፓርቲው መለያ አድርጎ የተቋቋመው የዲሞክራቲክ ፓርቲ ሁለቱም ወደ ሁለት ክፍለ ዘመን የዕድሜ ጣሪያ በመሸጋገር ከዓለማችን “ሽበቶ” ፓርቲዎች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ሊሆኑ በቅተዋል። እነርሱን የሚቀድሙ ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቢኖሩም የስልጣን አቀበቱን ተቋቁመው ማሸነፍ ስላልቻሉ በግብራቸው ሳይሆን ስማቸውን እንዳስከበሩ በታሪካቸው ርዝመት ብቻ “አንቱ” እንደተባሉ ዘልቀዋል።

የእንግሊዞቹ የኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ እ.ኤ.አ በ1834 መመስረቱን ስናነብና ስንሰማ “ወይ ነዶ! በዕድሜያቸው የከበሩ፤ በፍሬያቸው የጎመሩ ሀገራዊ ፓርቲዎች እንዳይኖሩን በእኛ የፖለቲካ ባህል ላይ እጅ-ሰብ የመተተብን ማን ይሆን?” በማለት በመንፈሳዊ ቅንዓት ብንንተከተክ አይፈረድብንም።

እ.ኤ.አ በ1912 የተመሠረተው የደቡብ አፍሪካው የአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት የመቶ ዓመት የእድሜ ሻማውን ሲለኩስ በበዓለ ልደቱ ላይ የታደሙት የእኛዎቹ “የፖለቲካ መሪዎች” ምን እንደ ተሰማቸው እንዲመሰክሩ በሞጎደኞቹ የዚያች ሀገር ጋዜጠኞች ያለመሞገታቸው ዕድለኛ አድርጓቸዋል። “የሺህ ዘመናት ስልጡን ነኝ ባዩዋ የእናንተይቱን ኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች እድሜያቸው እንዳይረዝም የሚያመክነው ጨንጋፋ ስሪት ምንድን ይሆን?” ተብለው ሳይፋጠጡ በመቅረታቸው እነርሱን ሳይሆን እኛን ይቆጨናል። መች ያኔ ብቻ ዛሬም “እንደተወለዱ የሚሞቱ” የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመብዛታቸው የተነሳ “ቀብራቸው በወጉ ባለመፈጸሙ” በርካታ አባል ተብዬዎቻቸው ከእነእርማቸው እንዳሉ አሉ።

**የሀገራዊ ፓርቲዎቻችን እና የትራፊክ ምልክቶች ተመሳስሎ**

በርካቶቹ የመንገድ ዳር የትራፊክ ምልክቶች በባህርያቸው ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ናቸው። የመልእክቶቹ ይዘት በአብዛኛው “አድርጉ ወይንም አታድርጉ” በሚል ሕግ ዙሪያ የታጠረ ነው። አንዳንድ ምልክቶች የአስገዳጅነት ባህርይ ሲኖራቸው፤ አንዳንዶችም ቀድመው የሚያስጠነቅቁ ናቸው። የመከልከልና የመወሰን ስልጣን ያላቸው ምልክቶችም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

በምሳሌ እናብራራው፡- አንዳንድ ምልክቶች አሽከርካሪው የተሳሳተ መንገድ ውስጥ እንዳይገባ ወይንም ምልክቶቹ የሚያስተላለፉትን መልእክት በቸልታ እንዳይመለከት ያስጠነቅቃሉ። አንዳንዶችም ከፊት ለፊት አደገኛ መንገድ ወይንም ችግር የሚያስከትሉ መሰናክሎች እንደሚኖሩ ይጠቁማሉ። ትክክለኛውን መንገድ መልቀቅ እንደማይገባው ቀድመው የሚያስጠነቅቁ ምልክቶችም የተለመዱ ናቸው።

ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ ወይንም አደባባዮችን በአግባቡ ለመዞር ፍቃድ የሚሰጡ ዓይነት ምልክቶችም የተለመዱ ናቸው። ለእነዚህ መሰል አስገዳጅ፣ መካሪና አስጠንቃቂ ምልክቶች ባዕድ ሆኖ በግዴለሽነት ከቤቱ የሚወጣ አሽከርካሪ ምን ገጥሞት እንደሚውል ለመገመት አይከብድም። “አሽከርክር ረጋ ብለህ” የሚለው ሀገራዊ ዝማሬ እንደ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊታወስ የሚገባው የጋራ አዋጅ ነው።

አደባባዮችን ከግራ ወደ ቀኝ (Clockwise) መዞር በሚፈቅዱ ሀገራት ሲያሽከረክር የኖረ ሾፌር ሕጉ ከቀኝ ወደ ግራ (Unticlockwise) በሚፈቅድባቸው አካባቢዎች ሲገኝ መተግበር የሚገባው የታዘዘውን ሕግ እንጂ “እኔ እኮ በኖርኩበት ሀገር...” እያለ በመፎከር ከሥርዓቱ ጋር ቢላተም ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚገባው ምናልባትም ነፍሱ ከህልፈት ተርፋ ካገገመ በኋላ ሊሆን ይችላል።

የትራፊክ መብራቶችም ቢሆኑ ለሃያ አራት ሰዓት እየተፈራረቁ የሚያጋፍሩት አሽከርካሪዎቹ እንደ ርችት ቀለማቱን እያዩ እንዲዝናኑ ሳይሆን ሕጉ እንዲከበር ማዘዛቸው ነው። “ጉዳዬ አጣዳፊ ስለሆነ የመብራቶቹን ትዕዛዝ ለመፈጸም ትእግስት የለኝም” ብሎ የሚወስን አሽከርካሪ ያለምንም ጥርጥር የመቀበሪያ ጉድጓዱን እየቆፈረ መሆኑ ይጠፋዋል ተብሎ አይገመትም።

ይህንን መሰል ዝርዝር የመንገድ ዳር የትራፊክ መርህ ለመተንተን የተፈለገው ለአሽከርካሪዎች ትምህርት ለመስጠት ታስቦ ሳይሆን የሀገራችንን ፖለቲካ የሚዘውሩ የፓርቲዎች ጉዞ ከዚህ የእለት ተእለት ክስተት ጋር በእጅጉ የሚቀራኝ ስለመሰለን ነው።

አብዛኞቹ “ደርሶ ሂያጅ” የሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በጽንስ ደረጃ የሚቀጩት ወይንም ብዙ ርቀት ሳይጓዙ ጠውልገው ሲሞቱ የምናስተውላቸው ከአፈጣጠራቸው ጀምሮ የስሪታቸው ውቅር “በጥቁር ደም” የበቀል ርዕዮተ ዓለም ተነክረው ስለሚወለዱ ይመስላል። ለክፋቱ ደግሞ “የደሙን ሸማ” የሚጠቀልሉት በኢትዮጵያ ስምና በዲሞክራሲ ቅጽል መሆኑ ነው።

“ደም የጠራው” እንዲሉም፤ ገና ከጅምሩ አዲስ የተወለደው ፓርቲ ከእርሱ ቀድሞ ድክ ድክ የሚለውን ጨቅላ ፓርቲ ጡጦውን ካላስጣልኩ ብሎ ከመተቸት አልፎ ተርፎ “ሻምላ መዝገቤ ካልተፋለምኩት” በማለት የፖለቲካ ምህዳሩን ወደ ግዳይ ወረዳነት ስለሚለውጠው “የሟችም ሆነ የገዳይ ፓርቲዎቹ ፍጻሜ” የሚጠናቀቀው ከዚያው ከሞት ሸለቆ ውስጥ ሳይወጡ ይሆናል።

የሕዝቡን ሥነ ልቦናና ስሜት ከማጥናትና ከማክበር ይልቅ ያለፍላጎቱና ያለውዴታው “የብሔሩን ስም እንደ ማጌጫና ጋሻ ለመጠቀም” የሞከሩ ፍጻሜቸው እንዴት እንደተደመደመ አይጠፋንም። በቀኝና በግራ መንገደኛነት “የትራፊኩን ሕግ በመጣስ” በርእዮተ ዓለማቸው ጋቢና ውስጥ ሆነው ህመምተኛውን ፖለቲካቸውን ሲዘውሩ የነበሩ የትናንት ከትናንት ወዲያ ስብስቦች ፍጻሜምም በምን እንደ ተደመደመ ያልመሸበት ታሪካችን ምስክር ነው።

በርካታ ደፋር የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የመጀመሪያውን የመቋቋሚያቸውን “አዋጅ” ይፋ ሲያደርጉ የኖሩትም የብሔረሰቦችን ያደረ ወይንም የመሸበትን የቁርሾ ትርክት በመዘርዘር ሙሾ እያሞሹና ሙሾ አውራጆችን እያሰባሰቡ ሰላማዊውን ሕዝብ “ተነስ፣ ታጠቅ፣ ዝመት” በሚሉ መፈክሮች ሞራሉን እያጋጋሉ እንደነበር ደጋግመን አስተውለናል። ዛሬም ወደ ቀልብያቸው ተመለሰው እንደሆን እርግጠኞች አይደለንም።

አንዳንዶችም ገና ከማለዳው ሕጋዊ የሚሰኘውን “ማህተማቸውንና ሰነዳቸውን” በእጅ ቦርሳቸው ውስጥ አጭቀው ርእዮተ ዓለማቸውን የሚያስተዋውቁት “መደበኛውን ፖለቲካዊ የትራፊክ ሕጎች እየጣሱና አባላቶቻቸውም እንዲጥሱ እያበረታቱ ጭምር ነበር።” ይህን መሰሉ “የጠብ ያለሽ ፖለቲካ” ጅማሮ ዛሬ ዛሬ ቀርቷል የሚለን ተሟጋች ብናገኝ ደስታው እያስፈነደቀን “ስለ ብዕራችን የአፍ ወለምታ” ንሰሃ ለመግባቱ አይከብደንም ነበር።

አንዳንዶችም አሉ፡- ከቀደምት የፖለቲካ ጠባሳቸው ገና ሳያገግሙ ለድጋሚ “ዓላማ ቢስ ፍልሚያ” መሪዎቻቸው ግፋ በለው እያሰኙ በማስፎከር “ቀይ መብራት እንዲጥሱ” የሚያበረታቱ። እንዲህ ዓይነቱ በሽታ የተጠናወታቸው “የፓርቲ መሪዎች ተብዬ” የማይገባውን ድንበር ካላለፍን፣ የማይፈቀደውን ካልጣስን፣ የተከለከለውን ካልሞከርን ወዘተ. እያሉ ተጓዦችን አግተልትለው ሲጓዙ መና ቀርተው መና ያስቀሩም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ “የደም ውርስ ሾተላይ” ያለበት ይመስል ለመጨንገፍ እጅግ ቅርብ ነው። ተጀምሮ ያልከሸፈ፣ ለመዋሃድ ተማምለው ያልተበተነ የፓርቲዎች ስብስብ አለ የሚል ምስክር ከተገኘ ደግመን የምናረጋግጠው እርሱን ለመስማት፣ እኛም ለሰነዘርነው ሃሳብ “አፉ በሉን - ስሜት አሳስቶን ነው!” ለማለቱ አናፍርም፤ አንሸማቀቅምም።

የፖለቲካችን ምህዳር እብቅ እንጂ ፍሬ አልባ የመሆኑ ጉዳይ በአግባቡ ተመርምሮ መፍትሔ እስካልተገኘለት ድረስ ጭንገፋው ባህል ሆኖ መቀጠሉ አይቀሬ ነው። እንዲያው ለማሳያነት እንዲረዳ በነበር የሚዘከሩትንም ሆነ ዛሬም ድረስ እስትንፋሳቸው ሊጨልም ጭል ጭል የሚሉ የፖለቲካ ቡድኖችን የሚመሩ ፊት ቀደሞቻቸውን በየሚዲያው አየር ላይ ብቅ ሲሉ ልብ ብለን እስቲ እናድምጣቸው፤ እናስተውላቸውም።

ገና መድረኩን እንደተቆጣጠሩ አንዳች የሚያንዘረዝር በሽታ ያለባቸው ይመስል ሌላውን ማጠልሸት፣ መወራጨት፣ መተቸት፣ መዘርጠጥ ልማድ አድርገውታል። ረጋ ብሎ፣ ሰክኖና ሃሳብን በአግባቡ አደራጅቶ የማስረዳት አቅም ሲጎላቸው ፈጥነው የሚሸጋገሩት ወደ “መቧቀስ ነው!” የገዢውን ፓርቲ ጥንብ እርኩስ ማውጣት፣ የተቀሩትን ተፎካካሪ ፓርቲዎች እንዳልባሌ መቁጠር ወዘተ. ጨዋታው እንዲህ ነው።

የገዢው ፓርቲ ሰዎችም ቢሆኑ ከዚህን መሰሉ ወረርሽኝ የተላቀቁ አይመስልም። የራስን ስኬት በራስ ዐውድ መጥኖ “እወቁልኝ፣ አመስግኑኝ” ከማለት ይልቅ ከቀደምት ሙታን የፖለቲካ ቡድኖች ጋር ራሳቸውን ማወዳደራቸውን “የእነርሱን ቤተኞች” ባናውቅም አብዛኛው ሕዝብ ግን ይህንን ባህርያቸውን የወደደላቸው አይመስልም። “የፖለቲካውን የትራፊክ ሕግ” በመጣስ ረገድ ሥልጣን የተቆናጠጠው ፓርቲም ቢሆን “ከደሙ ንፁህ ነኝ!” ብሎ የማይሟገትባቸውን በርካታ ጥሰቶች ሲፈጽም እያስተዋልን ስለሆነ ቢታረም አይከፋም።

በተለይም ይህን ያህል ሚሊዮን አባላት አለኝ “የሚሉት ፉከራ” በመሪነት በትሩ ሥር የተጠለሉትን ተራ የእለት እንጀራ ፈላጊ ዜጎች እንዴት እንደሚያበግናቸው ቢረዳው መልካም ይሆናል። ካሻቸው እዚያው በቤታቸው ቁጥሩን እየጠቀሱ “ዋንጫ ኖር!” ይበሉ እንጂ በሕዝብ ሚዲያና መድረክ ብቅ ባሉ ቁጥር “ይህንን ያህል አባላት አለን” የሚለውን ትምክህት ባይለማመዱት ይበጃቸዋል።

ይህንን የምንለው “ከሚሊዮኖቹ የገዢው ፓርቲ አባላት” መካከል ብዙዎቹ በሥራና በሕይወታቸው ውስጥ ቅጠላቸው ተንዠርግጎ ካልሆነ በስተቀር ከየግል የኃላፊነት አተገባበራቸውና የውሎ መስካቸው ፍሬያቸውን በገሃድ ለማየት ስላልቻልን ነው። በየመስኩ ሲባዝኑ፣ ሲወጡና ሲወርዱ፣ ሲሰደቡ ወይንም ሲመሰገኑ የምናያቸው ጥቂቶቹን “አንቱዎች” ብቻ ነው። እነዚያ ሚሊዮን አባላት በየመንግሥታዊ ተቋማት የተገለጋዩን እምባ ሲያብሱ፣ በተግባራቸው ምሳሌ ሆነው ሲጠቀሱስ፣ ከጉቦና ከዘረፋ ነፃ ሆነው ሲመሰገኑ አድምጠናል? መልሱን እያወቅን የምናልፈው በሆድ ይፍጀው የተለመደ ብሂላችን ይሆናል።

ለማንኛውም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመጨንገፍና ከሾተላይ ሕመም እንዲፈወሱ ካስፈለገ ይደማመጡ፣ ሲፎካከሩም ይከባበሩ፣ ሲተቻቹም እርስ በእርስ በመተናነጽ ይሁን እንጂ በነገር ጎራዴ እየተሞሻለቁ አይተላለቁ። እነርሱ ብቻ ለሀገር የሚያስቡ፤ እነርሱ ብቻ ለሕዝብ ጽድቅ “ቅባ ቅዱስ የተቀቡ” ነፃ አውጪ አድርገው ራሳቸውን በራሳቸው ከማጽደቅም ይፈውሱ። መልእክቱ ይሄው ነው። ሰላም ይሁን!

# ጤናማ የግብይት ሰንሰለት ያስመዘገበው ውጤት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ከምታቀርባቸው በርካታ የግብርና ምርቶች መካከል አረንጓዴ ወርቅ የተባለው ቡና በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዘንድሮው የበጀት ዓመት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአስር ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ወደ ውጭ ገበያ ከተላከው ቡና ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት እንደተቻለ ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ከሰሞኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ላለፉት ሰባት ተከታታይ አመታት አጠቃላይ ኤክስፖርቱ እድገት ያላሳየ እንደሆነና በአሁኑ ወቅት አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ በተለይም ቡና ከፍተኛ እምርታ ማስመዝገብ የቻለ መሆኑን አንስተዋል።

ቡና በዘንድሮው በጀት ዓመት እምርታ ያሳየ ስለመሆኑ እና በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በቡና ልማትና ግብይት የተመዘገበው ውጤት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ቡና በስፋት እየተተከለ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነም አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ ለዘመናት እየተፈተነችበት ያለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ማቃለል የምትችለው ወደ ውጭ ገበያ በምትልከው ምርቶች በመሆኑ ምርታማነት ላይ አተኩሮ መሥራት የግድ እንደሆነም አመላክተዋል። ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም በተለይ በግብርናው ዘርፍ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ተግባራዊ በማድረግ በርካታ ጠቀሜታዎችን ማስመዝገብ የቻለና በቀጣይም ውጤታማ ሥራ ሊሠራበት የሚገባ እንደሆነም ይታመናል።

ቡና በአሁኑ ወቅት ትርጉም ያለው ለውጥ እያስመዘገበ ያለና ለአገር ኢኮኖሚም በጎ አስተዋፅኦውን እያበረከተ ይገኛል። ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደጠቀሱት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ተግባራዊ በማድረግ ቡና በስፋት መተከል መቻሉ አንዱ ሲሆን በግብይት ሰንሰለቱም የተሠሩ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ስለመኖራቸው ባለሙያዎች ያነሳሉ።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቡና ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የጀመረው ካለፈው ዓመት ጀምሮ እንደሆነና ለዚህም መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ያነሱት የቡና አምራቾች ማህበር ፕሬዚዳንት ዶክተር ሁሴን አምቦ ናቸው።

እንደሳቸው ማብራሪያ፤ በቡና የግብይት ሰንሰለት ውስጥ ይስተዋሉ የነበሩ ብልሹ አሠራሮችና በሕገወጥ ንግድ ዙሪያ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በርካታ ሥራዎችን እንደሠራ ነው ያነሱት። በተለይም ቡና አልሚዎች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ኢሲኤክስ) ሳይገቡ ደረጃውን የጠበቀ ቡና በቀጥታ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲችሉና ዘርፉ ከምርት ገበያው ውጭ መሆኑ አሁን እየታየ ያለውን ውጤት ከማስመዝገብ ባለፈም አርሶ አደሩም በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከፍተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል።

የኢትዮጵያን ቡና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ካደረጉት ጉዳዮች መካከል አንዱ የ‹‹ካፕ አፍ ኤክሰለንስ›› መርሃ ግብር ነው። በቡና ግብይት ሰፊ ድርሻ ባለው በካፕ አፍ ኤክሰለንስ ፕሮግራም ትልቅ መሻሻል ታይቷል። ይህም ለዘርፉ ውጤታማነት ሁለተኛው ምክንያት ነው። ፕሮግራሙ በተለይም ገበሬውን ከጉድጓድ አውጥቶ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆን አስችሎታል።

በጥራት የተዘጋጀው ቡና ለውጭ ገበያ እየቀረበ ገበሬው የተሻለ ገቢን እያገኘ ሲሆን በተለይም በአሁኑ ወቅት በታሪክ ከ50 ብር ተሻግሮ የማያውቀው አንድ ኪሎ ጀንፈል ቡና በአሁኑ ወቅት እስከ 150 ብር ደርሷል። ለዚህም በግብይት ሰንሰለቱ መሀል ገብቶ ጥራቱንና ዋጋውን የሚበጠብጥ አካል ባለመኖሩ ነው።

ይሁንና ቡና ከፍተኛ ትኩረት፣ ክትትልና ቁጥጥር የሚፈልግ በመሆኑ ችግሮች ሲፈጠሩ በቶሎ ለችግሮቹ መፍትሔ በመስጠት ዘርፉ እያስመዘገበ ያለውን ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ የግድ እንደሆነ ያነሱት ዶክተር ሁሴን፤ ለዚህም መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት መሠረት ከላይኛው አመራር ጀምሮ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ ባለሙያዎች በቅርብ ሆነው ልማቱንና ግብይቱን መከታተል ያለባቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ቡና በመጠን ሳይባከን ጥራቱም ሳይጓደል አርሶ አደሮች በቀጥታ ለአቅራቢዎች፤ አቅራቢዎች ደግሞ ለላኪዎች ማስረከብ የሚችሉበት አሠራር ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ዘርግቶ መስራት በመቻሉ በግብይት ሂደት የነበረውን የተንዛዛ አሠራር ማስቀረት ተችሏል። ከዚህም ባለፈ መነሻውና ምንነቱ የታወቀ የቡና ምርት ለዓለም ገበያ በማቅረብ የኢትዮጵያ ቡና የተሻለ ዋጋ እንዲያወጣ የራሱን አስተዋጽኦ ተጫውቷል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ግብይቱን የማዘመንና ፍትሃዊ የማድረግ እንዲሁም እሴት የመጨመር ተግባርን በማከናወን አገሪቷ ከዘርፉ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንድትችል ግብ ይዞ እየሠራ መሆኑን የገለጹት በቡናና ሻይ ባለስልጣን የገበያ ልማትና ቁጥጥር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር ናቸው። እንደሳቸው ገለጻ አጠቃላይ ግቡን ሊያሳኩ የሚችሉ ተግባራት መከናወናቸውን ሲያስረዱ፤ የኢትዮጵያ ቡና በተለይም በአሁኑ ወቅት ላስመዘገበው ውጤት ምርቱ ሳይባክን ከምርት እስከ ኤክስፖርት መዳረሻ ድረስ በትክክል መውጣት የሚያስችለውን ሥራ መሥራት በመቻሉ እንደሆነ አንስተው፤ በአሁኑ ወቅት ከዘርፉ የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት መመዝገብ እንዲችል አስቻይ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ከሠራቸው ሥራዎች መካከልም አንደኛው አገራዊ ግብረ ኃይልን የማጠናከር ሥራ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደራሽ ቁጥጥር በማድረግ ቡና እንዳይባክን ማድረግ ተችሏል። ሦስተኛው በሶፍትዌር ሲስተም በመገንባት ሁለቱን በመደገፍ ቡናው ሳይባክንና ከመጣበት ቦታ በቀጥታ ወደ መዳረሻው እንዲደርስ የማድረግ ሥራ ነው።

ከግብረኃይል አንጻር በተለይም ከፌዴራል ፖሊስ፤ ከጉምሩክ ኮሚሽን፤ ከአዲስ አበባ ከንግድ ቢሮ፤ ከኦሮሚያ፣ ከደቡብ ምዕራብና ከሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን የተጠናከረ የቅንጅት ኮሚቴ በማዋቀር ኮሚቴዎቹም ከታች ያሉትን ግብረኃይሎች በማጠናከር ትርጉም ያለው ሥራ ተሠርቷል።

እስካሁን በነበረው አሠራር የኢትዮጵያ ቡና የላላ ቁጥጥር የነበረውና በትክክልም ቡናው የት እንደደረሰ የማይታወቅበት ሁኔታ እንደነበር ያስታወሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በምርት ገበያ ላይ ኮንትሮባንዱ በዝቶ ቡናው ወደ አገር ውስጥ ይመለስ የነበረ መሆኑን አስታውሰዋል። ይሁንና በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን የነበሩ ችግሮችን ማቃለል ችሏል። በተለይም የተለያዩ የጥራትና ቁጥጥር ሶፍትዌሮችን በመገንባት የአገሪቷ ቡና የት እንደሚገኝ፤ ከየት እንደተሰበሰበና የት እንደደረሰ በመከታተል እርምጃ እየወሰደ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ጥራት ያለውን ምርት ማምረት፤ ግብይቱን ዘመናዊ ማድረግ፤ የዘርፉ ተዋናዮችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥና በዚህም አገሪቷ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት እንድትችል በማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

የምርት ጥራትን በተመለከተ በቀዳሚነት አርሶ አደሩ ጋር ያለውን ክፍተት የመድፈን ሥራ እየተሠራ ነው። ለአብነትም ካፕ አፍ ኤክሰለንስ ለሦስተኛ ዙር እየተካሄደ ነው። ምርቱን በጥራት በማምረት የተሻለ ገቢ እንዲገኝ እየተሠራ ሲሆን ከዚህም ባለፈ አርሶ አደሮች የራሳቸውን ምርት በቀጥታ ወደ ውጭ ገበያ መላክ የሚችሉበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ከካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ በተጨማሪም ወደ ውጭ ገበያ የሚላከው ቡና እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት አርሶ አደሩ ዕውቀት እንዲኖረው ያስችለዋል።

ግብይቱን በማዘመን በተለይም በግብይት ሰንሰለት ውስጥ የነበረውን አላስፈላጊ ሂደት በመቁረጥ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲፈጠርና አርሶ አደሩ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከዚህም ባሻገር አገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ውጤት እንድታገኝ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን አንስተዋል።

ቀልጣፋና ዘመናዊ የግብይት ሂደት በመፍጠር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ቡና በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል ተደርጓል። ይህ ውጤት ሊመዘገብ የቻለውም በሁለት ምክንያቶች እንደሆነ በመግለጽ፤ አንደኛው የነበሩ ችግሮችን ለይቶ ለማውጣት ሪፎርም የተካሄደ ሲሆን ሁለተኛው ሪፎርሙን ሊደግፉ የሚችሉ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መሻሻላቸው እንደሆነ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

በዚህ ሂደትም ከዚህ ቀደም አርሶ አደሩ ቡናውን የሚሸጠው ለደላላ ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ስድስት አማራጮች ተቀምጠውለት በሚያመቸው መንገድ መሸጥ እንዲችል ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረውለታል። ስድስቱ አማራጮችም አንደኛው በምርት ገበያ፣ ሁለተኛው ለአቅራቢ፣ ሦስተኛው ከአካባቢው ባለሀብት ጋር በመተባበር በተሻለ ዋጋ መሸጥ የሚችልበት አማራጭ ሲሆን፤ አራተኛው አርሶአደሩ ፈቃድ አውጥቶ በቀጥታ ቡናውን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ይችላል። አምስተኛ ከህብረት ሥራ ዩኒየን ጋር በጋራ በመደራጀት በዩኒየኑ አማካኝነት ቡናውን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ይችላል። ስድስተኛውና የመጨረሻው አማራጭ ለቡና ቆይዎች ቡናውን መሸጥ የሚችልበት አማራጮች ናቸው።

እነዚህ ሁሉ የገበያ አማራጮች ከዚህ ቀደም ያልነበሩና በሪፎርሙ የመጣ ለውጥ እንደሆነ የጠቀሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሩ በአካባቢው ለሚገኝ ባለሀብት ቡናውን በመሸጡ ከባለሀብቱ በርካታ አገልግሎቶችንና ድጋፍ ያገኛል። ለአብነትም አዳዲስ ዝርያዎችን ከማግኘት ባለፈ የቴክኖሎጂ ሽግግር ያደርጋል። አርሶ አደሩ ከባለሀብቱ በሚያገኘው ድጋፍም የተሻለ ምርት በመሰብሰብ በተሻለ ዋጋ ቡናው የሚሸጥ ሲሆን በዚህም አርሶ አደሩን ጨምሮ ባለሀብቱና አገሪቷም ከዘርፉ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ።

ሌላው ካለፈው ዓመት ጀምሮ በዘርፉ ከፍተኛ ለውጥ እንዲታይ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል የላኪና አቅራቢ ግንኙነት አንዱ ነው። በላኪና አቅራቢ መካከል የነበሩና ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨምሩ ተጠቃሚ ሆነው የቆዩ ሰንሰለቶችን ማስቀረት ተችሏል። እነዚህ በመካከል የገቡ አላስፈላጊ አካላትን ማስወገድ መቻሉ አንደኛ የቡና ጥራት እንዲኖር አስችሏል።

የቡና ጥራትን በተመለከተ ባለፈው ዓመት ደረጃ አንድ ቡና 83 በመቶ ጥራቱን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን፤ ደረጃ ሁለት ስድስት በመቶ፣ ደረጃ ሦስት 44 በመቶ፣ ደረጃ አራትና አምስት ደግሞ ዝቅተኛ ሆኖ ተመዝግቧል። ደረጃ አንድ፣ ሁለትና ሦስት ቡና ሲሸጥ ጥራት ያላቸው በመሆናቸው በድርድር በከፍተኛ ዋጋ ይሸጣሉ። ይህም በቀዳሚነት የቡና ጥራት እንዲጠበቅ ከማስቻል ባለፈ አርሶ አደሩ ፍትሃዊ ተጠቃሚ በመሆን ቡናውን በተሻለ ዋጋ እየሸጠ ይገኛል።

ከዚህ ቀደም በኪሎ 10 ብር ሲሸጥ የነበረው ቀይ እሸት ቡና በአሁኑ ወቅት እስከ 50 ብር እየተሸጠ ይገኛል። ጀንፈል ቡና ደግሞ ከ100 ብር በላይ ደርሷል። አርሶ አደሩ ከዚህ ቀደም ቡናውን በዚህ ዋጋ ሸጦ እንደማያውቅ ያነሱት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ አቅራቢው ቡናውን ከአርሶ አደሩ ገዝቶ ለላኪዎች ያቀርባል። ላኪውም ጥራት ያለው ቡና ሲቀርብለት በተሻለ ዋጋ ቡናውን ገዝቶ ወደ ውጭ ገበያ ይልካል። በዚህም ሳይተዋወቁ የቆዩት ላኪና አቅራቢዎች ተዋውቀው ተግባብተውና ተናበው እየሠሩ በመሆናቸው ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ከምርትና ምርታማነት እንዲሁም ከግብይት ሥርዓቱ በተጨማሪ ቡና ውጤታማ መሆን እንዲችልና አገሪቷም ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆን እንድትችል የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ ነው። ይህም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በተለይም ነባር ገበያ ውስጥ የመቆየትና አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን የማፈላለግ ሥራም እየተሠራ ነው ብለዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## እኛም ሕዝቦች አገር እንምራ!

**ዋለልኝ አየለ**

ስለልዕለ ኃያሏ አሜሪካ ብዙ ሰዎች የሚሉት አንድ ነገር አለ፤ በሆነ ድንገተኛ አጋጣሚ የአገሪቱ መሪ ባይኖር አገሪቱ ምንም አትሆንም። እንዲህ ዓይነት ትንታኔዎች የበዙት በተለይም ዶናልድ ትራምፕ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆነው ከመጡ በኋላ ነበር።

ዶናልድ ትራምፕን ብዙዎች እንደሚሏቸው፤ እንኳን አገርን ያህል ነገር፣ አንድ ተቋም የመምራት ስብዕና የሌላቸው ናቸው። ሆኖም ግን ኃያሏን አሜሪካን ለአራት ዓመታት አስተዳድረዋል። ግን አገሪቱ አሜሪካ ስለሆነች በእንደ ትራምፕ ዓይነት ሰው ተመራች። ለምን? ሕዝቡ የሰለጠነ ስለሆነ።

ትራምፕ የአንዲት አፍሪካ አገር መሪ ቢሆኑ ብለን እናስብ። ያቺ አገር እስከዛሬ አትፈርስም ነበር? የዓለም አገራት መሪዎች ሌላ ያወሩ ነበር? ማዕቀብ በማዕቀብ አትሆንም ነበር? ዳሩ ግን ማዕቀብ ጣይና አንሽዋ አሜሪካ ስለሆነች በእንደ ትራምፕ ዓይነት ሰው ተመርታለች። እነሆ ሌላም ምስክር!

በአሜሪካ የምርጫ ሕግ መሠረት የትራምፕ ጊዜ ገደብ ተጠናቆ ምርጫ ሲደረግ ከጆ ባይደን ጋር የነበረው ፉክክር የዓለምን ቀልብ ስቦ ነበር። ትራምፕ ግን ገና ምርጫው ሳይደረግና የምርጫው ውጤት ሳይታወቅ ነበር «ተጭበርብሯል፣ እከሳለሁ» የሚል ድንፋታ የጀመሩት።

በዚያን ወቅት የተለያዩ የዓለም መገናኛ ብዙኃን የሕዝብ አስተያየት እያሰባሰቡ ነበር፤ «እንዴት አሜሪካ ውስጥ ሆኖ ምርጫ ተጭበርብሯል ይላል! አስደፈረን!» እያሉ በቁጣ የሚናገሩ ብዙዎች ነበሩ። እንዲህ ዓይነት ስብዕና ባለው ግለሰብ ስትመራ የቆየችው አሜሪካ ምንም ኮሽታ ሳይፈጠር ጣጣዋን ጨረሰች።

የአሜሪካን ነገር ያነሳሁት ስለአሜሪካ ለማውራት አይደለም። የሕዝብ መሰልጠንና ለአገር አሳቢነት ምን ያህል አገርን ሰላም እንደሚያደርግ ምሳሌ እንዲሆነን በሚል ነው።

እውነት እኛ የኢትዮጵያ ሕዝቦች እንደሚባልልን ስልጡንና የምንከባበር ነን? በአፋችን እንደምናወራው አገር ወዳድ ነን? እንዲያ ከሆነ ታዲያ እነዚህ በየጊዜው የምናያቸው ዘግናኝ ድርጊቶች ከየት የመጡ ናቸው?

ሕዝብ ነው የሚያደርጋቸው ለማለት አይደለም፤ ዳሩ ግን ለድርጊቶች መቀጣጠል ድንጋይ አቀባዮች ነን። የንትርክና የጥላቻ ዘመቻውን አቀጣጣዮች ነን። አሉቧልታና የሀሰት መረጃዎችን ብንጸየፍ እንዲህ አይሆንም ነበር።

በነገራችን ላይ መንግሥት «ድብቅ አጀንዳ ያላቸው» የሚለው እውነት ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ጥፋት የሚያደርሱ ሰዎች በግልጽ አይታዩም። ያም ሆኖ ግን «ድብቅ አጀንዳ ያላቸው» የምትለዋ የተለመደች አገላለጽ መንግሥትንም ከወቀሳ አታድንም። በኢህአዴግ ጊዜ በጣም የተሰለቸ አገላለጽ የነበረው «የእገሌ ተላላኪዎች» የሚል ነበር። እነሆ አሁንም እየተባለ ነው። ጥፋቱን ያ የተባለው አካል ካደረሰው አስተዳዳሪው መንግሥት አይወቀስም ማለት ነው?

ሕዝብም እኮ እያለ ያለው መንግሥት ሕግ ያስከብርልን ነው እንጂ መንግሥት ራሱ ነው ጥፋቱን ያደረሰው አይደለም። «እገሌ ነው ጥፋቱን ያደረሰው» ማለት ከተወቃሽነት አያድንም። ምክንያቱም እነ «እገሌ» ጥፋት እንዳያደርሱ መጠበቅ የመንግሥት ኃላፊነት ስለሆነ። አሁን ያለው የአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። መንግሥት ሕግ የማስከበር ሥራ እየሠራ ነው።

አንድ የሚገርመኝ ነገር ግን የመንግሥት ችግር ተደጋግሞ ሲነገር የሕዝብ ችግር ደግሞ አለመነገሩ ነው። መንግሥትም ታዋቂ ሰዎችም አንድ ያስለመዱት ነገር አለ። ይሄውም «ሕዝብ ሁሌም ትክክል ነው» የሚባለው ነገር። ሕዝብ ሁሌም ትክክል ነው ብሎ መደምደም አይቻልም። ሕዝብም ይሳሳታል። መንግሥት እርምጃ ሲወስድም ይወቀሳል፤ ባለመውሰዱም ይወቀሳል። ምናልባት «ሕዝብ ማለት የትኛው ነው?» የሚለው ያወዛግብ ይሆናል። ምንም ይሁን ግን ሕዝብ ለሰላምና ለልማት ሆ ብሎ ቢነሳ ሰላም ማስፈን ይችላል። በአካባቢው የሚደርስን ጥፋት የማስቀረት ኃይል አለው። አካባቢውን የመጠበቅና ሰላም የማድረግ አቅም አለው።

የአገራችን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት መድረክ ላይ የሚያደርጉት ንግግር ብዙ ጊዜ አሰልቺና የተደጋገመ ነው ተብሎ ይወቀሳል፤ ግን አይፈረድባቸውም። ምክንያቱም ከተለመደው ወጣ ያለ ንግግር ቢጠቀሙ ብዙ ፀጉር ሰንጣቂ አለና ሌላ ጣጣ ማምጣት ነው ብለው ይፈራሉ። እየሆነም አይተናል። የከፍተኛ ባለሥልጣናት ንግግሮች በማህበራዊ ገጽ አልፈው በጋዜጣና መጽሔቶች፣ በሬዲዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች መነጋገሪያ ሆነው ያውቃሉ። ይሄ ችግር አልነበረውም (እንዲያውም ሀሳባዊነት ነው ልንለው እንችላለን)። ችግሩ ግን ወደ ጥፋት እየተገባ ነው። ከውይይት ይልቅ እንደ ድንጋይ ዘመን ወደ ድንጋይ ለቀማ እየሄድን ነው።

በነገራችን ላይ ይሄኛውም ችግር ወደ መንግሥት ይወስዳል። «በውይይት የሚያምን የሰለጠነ ሕዝብ መፍጠር የመንግሥት ኃላፊነት ነው» የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ግን ያ ደግሞ የእነዚያ የጠቢባን አባቶች ልጅ ሆኖ ከመንግሥት ብቻ መጠበቅም ትክክል አይደለም። መንግሥት እኮ ይቀያየራል፤ በቃ አንድ የሥርዓት ዓይነት ነው። ደርግ ሄደ ኢህአዴግ መጣ፣ ኢህአዴግ ሄደ ብልጽግና መጣ፤ ብልጽግና ሲሄድ ሌላ ይመጣል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አገርና ሕዝብ አለ። አገርን ለትውልድ የሚያስተላልፈው አንድ ሥርዓት ብቻውን ሳይሆን ይሄ ሕዝብ ነው።

ፖለቲከኞች፣ ታዋቂ ሰዎች፣ ተራው ሕዝብ... መንግሥትን ምሩ። መንግሥት በሕዝብ ይመራል። አለበለዚያ መንግሥት በኃይል ይመራናል። መንግሥትን መምራት ማለት ሕግን ማክበር ነው። መንግሥትን መምራት ማለት ከመንግሥት ጋር መሥራት ማለት ነው። ይሄ ማለት መንግሥት እንደፈለገው ሲያበለሻሽ ዝም ማለት አይደለም። ዳሩ ግን ሁልጊዜ መንግሥትን መውቀስ ብቻ መፍትሔ ማስመሰል መንግሥት በራሱ ውሳኔ ብቻ እንዲመራን ማድረግ ነው። ምክንያቱም መስማማት ከሌለ የሚሆነው ይኸው ነው።

የሕዝብ መሪነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ የሕዝብ የበላይነት የሚታወቀው ፀብ አጫሪዎች ጥፋት በሚያደርሱበት በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት ነው። የውጭ መገናኛ ብዙኃን እየሠሩት ያለውን ዜና አይተናል። ገመናችን በዓለም አቀፍ ደረጃ እየታየ ነው ማለት ነው።

«ጥፋት አድራሹ ጥቂት ቡድን ነው፤ ሕዝብ ምን ያድርግ?» ይባል ይሆናል። ግድየላችሁም ጎበዝ መፍትሔው ከሕዝብ ነው። አንዱ በአንዱ ላይ ጥላቻ የሚያሳድር ነገር አንናገር። የእገሌ ሕዝብ ነው እኔ ምን አገባኝ አንበል! የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ነው በዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ላይ ያደረሰው የምንል ከሆነ የጥፋቱ ተባባሪዎች ነን ማለት ነው።

ሌላው ደፈር ብለን ልንናገረው የሚገባው ነገር፤ መንግሥት ሕግ ያስከብር ብለን እንደወተወትነው ሁሉ፤ መንግሥት በጥፋተኞች ላይ እርምጃ ሲወስድ «በእገሌ ሕዝብ ላይ የተደረገ ዘመቻ» ማለት የለብንም። ያልታጠቁ ንጹሃንን የሚጨፈጭፍ አረመኔ ማንንም ሕዝብ ሊወክል አይገባም!

በአጠቃላይ፤ ደረጃው ይለያይ እንጂ አገር የመምራት ኃላፊነቱ የሁላችንም ነው። አቀጣጣይ ነገሮችን አለመናገር ሰላምን እንደማስከበር ነውና ሁላችንም ኃላፊነታችንን እንወጣ!

# ዓለም አቀፍ



## የአውሮፓ ኅብረት በሩሲያ የምግብ እና የማዳበሪያ አቅርቦቶች ግዢ ላይ ማዕቀብ አለመጣሉን አስታወቀ

ከሩሲያ ምግብ እና ማዳበሪያ መግዛት የሚፈልግ ማንኛውም አካል ማዕቀብ ሳይፈራ ግዢ መፈጸም እንደሚችል የአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ኃላፊ ጆሴፍ ቦሬል አስታወቁ።

ቦሬል ይህን ያሉት የአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ነው።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ በሩሲያ እና ዩክሬን መካከል በዘለቀው ወታደራዊ ግጭት ምክንያት ጥቁር ባህር ወደቦች ላይ የተያዘውን የዩክሬን ወጪ የእህል ንግድ ማስለቀቅ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ይመክራል ተብሎ ይጠበቃል።

እንደ ዓለም ንግድ ድርጅት መረጃ ከ22 እስከ 25 ሚሊዮን ቶን እህል በዩክሬን ወደቦች ተይዟል።

ምዕራባውያን የዩክሬንን የእህል ወጪ ንግድ ሩሲያ አግዳለች በሚል በተደጋጋሚ ውንጀላ አቅርበዋል።

ሩሲያ ደግሞ እህሉ በነፃ ንግድ በጥቁር ባህር ወደቦች በኩል ለዓለም እንዲደርስ እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን ዩክሬን በባህሩ ላይ ካላት ልዩ ፍላጎት የተነሳ ወታደራዊ ኃይሏ ወደቦቹን በመቆጣጠሩ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል ማለቷን አር ቲ ኒውስ ዘግቧል።

ከአውሮፓ ኅብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባም የአውሮፓ ሀገራት ተጨባጭ ውጤት እየጠበቁ ይገኛል መባሉን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

## የካሜሮኑ ኮከብ ሳሙኤል ኢቶ 3.2 ሚሊዮን ፓውንድ ግብር ማጭበርበሩን አመነ

የቀድሞው የካሜሮን ብሔራዊ ቡድን አጥቂና የባርሴሎና ሁነኛ ተጨዋች የነበረው ሳሙኤል ኢቶ 3.2 ሚሊዮን ፓውንድ የግብር ማጭበርበር ውስጥ እጁ እንዳለበት አመነ። የአራት ጊዜ የአፍሪካ ኮከብ ተጨዋች የተባለው ኢቶ ትናንት ሰኞ በስፔን ፍርድ ቤት ቀርቦ የ22 ወራት በእግድ የሚቆይ ፍርድ ተፈርዶበታል።

ይሁንና ያጭበረበረውን ገንዘብ እና ተጨማሪ 1.55 ሚሊዮን ፓውንድ ቅጣት ጋር ደምሮ መመለስ ይኖርበታል። አቃቢ ሕግ ሳሙኤል ኢቶ ከማስታወቂያ ጋር በተያያዘ ያገኘው የነበረውን ገቢ ደብቆ ቆይቷል ሲል ነው የከሰሰው። ይህም በፈረንጆቹ ከ2006 እስከ 2009 ድረስ የቆየ የማጭበርበር ድርጊት ነው።

ኢቶ በተመሳሳይ ክስ ሲከሰስ ከውጭ ተጫዋቾች የመጀመሪያው አይደለም። ላለፉት ዓመታት በተመሳሳይ ከግብርና ገቢ ስወራ ጋር በተያያዘ ክርስቲያኖ ሮናልዶ፣ ሊዮነል ሜሲ፣ ጆሴ ሞሪንሆ እና ኔይማር ተመሳሳይ ክስ ውስጥ አልፈዋል።

የ41 ዓመቱ ሳሙኤል ኢቶ አሁን የካሜሮን ብሔራዊ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሲሆን ባርሴሎናን የተቀላቀለው በ23 ዓመቱ፣ በ2004 ነበር። ኢቶ ከባርሴሎና ሌላ ለሪያል ማድሪድ፣ ለኢንተር ሚላን፣ ለቼልሲ እና ኤቨርተን ቡድኖች ተጫውቷል። ኢቶ ከምሥል ጋር የተያያዘውን መብቱን ሐንጋሪ አገር ለሚገኝ አንድ ኩባንያ ያስተላለፈ ሲሆን ይህንን ያደረገው ግን በዚያ አገር የግብር ተመኑ ከሁሉም የአውሮጳ አገር ዝቅተኛ በመሆኑ ነበር።

ሳሙኤል ኢቶ ለፍርድ ቤት ማጭበርበሩን ካመነ በኋላ ባደረገው የክስ ማቅለያ ንግግር፣ «የተከበረውን ፍርድ ቤት መረዳት ያለበት ያን ጊዜ ልጅ ነበርኩ፤ ሁሉንም ነገር አደርግ የነበረው በተወካዬ ማሪያ ማሳሌስ አማካኝነት ነበር» መባሉን ቢቢሲ ዘግቧል



**ከኢፌዲሪ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ዘወትር ረቡዕ እና ቅዳሜ የሚታተም**

# በየጊዜው ምርመራ በማድረግ ቫይረሱ "የማይታይ" ሆኖ መቆየቱን ያረጋግጡ

**ዳንኤል ዘነበ**

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው ቦሌ 17 ጤና ጣቢያ ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው የሚገኝ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሕክምና ክትትላቸውን ያደርጋሉ። ጤና ጣቢያው በታካሚዎቹ ጠንካራ የመድኃኒት ቁርኝት በመፍጠር እንዲሁም የቫይረስ መጠንልኬት በማስጠበቅ ረገድ ውጤታማ ሥራን መሥራት ችሏል። እኛም በዛሬው እትማችን በቦሌ 17 ጤና ጣቢያ ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው ለሚገኝ ታካሚዎች ስለሚደረገው የሕክምና ክትትል፣ በተቋሙ ክትትላቸውን የሚያደርጉ ታካሚዎች የመድኃኒት ቁርኝት ሁኔታ፣ ታካሚዎቹ በደም ውስጥ ያለውን የቫይረስ መጠን በዘላቂነት ለመቀነስ ምን እያደረጉ እንደሆነ እና ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በተቋሙ የሕክምና ባለሙያ የሆኑት አቶ ፀጋዬ በቀለ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተውናል። አቶ ፀጋዬ የተቋሙን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የሰጡንን ማብራሪያ እንዲህ አዘጋጅተነዋል። መልካም ንባብ።

**የመድኃኒት ቁርኝትን ማስጠበቅና ውጤቱ**

በጤና ተቋሙ ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው የሚገኝ የተለያዩ ታካሚዎችን ክትትል ያደርጋሉ። ታካሚዎቹ በአገልግሎቱ ቢያንስ ከ10 ዓመት በላይ የጸረ - ኤች. አይ. ቪ. መድኃኒታቸውን የወሰዱ ናቸው። ይህ በመሆኑ የመድኃኒታቸው ቁርኝት ጥሩ ነው። ምክንያቱም ሕክምናቸውን በአግባቡ ይከታተላሉ፣ መድኃኒታቸውንም ሰዓቱን በጠበቀ መልኩ ሳያቋርጡ ይወስዳሉ። በተጨማሪም የሚታዘዝላቸውን የምርመራ ዓይነቶች እንደየ አስፈላጊነቱ መጥተው ያሠራሉ። የሕክምና ሳይንሱ አንድ ሰው በትክክል መድኃኒት የሚጠቀም ከሆነ በደም ውስጥ የሚገኝ የቫይረስ ቁጥር እየቀነሰ ይመጣል ይላል። ምክንያቱም ቫይረሱ በደሙ የሚገኝ ሰው

> **ታካሚዎቹ በአገልግሎቱ ቢያንስ ከ10 ዓመት በላይ የጸረ - ኤች. አይ. ቪ መድኃኒታቸውን የወሰዱ ናቸው።**

በትክክል መድኃኒቱን የሚወስድ ከሆነ የቫይረሱ ደረጃ የማይታይ መጠን ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቫይረሱ ከማይታይበት ደረጃ በታች የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። ከዚህ አኳያ በጤና ተቋሙ ሕክምናቸውን የሚከታተሉ ታካሚዎች በደማቸው ውስጥ የሚገኘውን የኤች. አይ. ቪ ቫይረስ ወደ ማይታይ መጠን ማድረስ ችለዋል። ይህም የሆነው ታካሚዎቹ በትክክል መድኃኒቱን መጠቀም በመቻላቸው ነው።

**የቫይረስ መጠን ልኬት**

በጤና ተቋሙ ክትትል የሚያደርጉት ታካሚዎች በትክክል መድኃኒታቸውን ከመውሰድ በተጓዳኝ በየዓመቱ የቫይረስ መጠን ምርመራ በማድረግ ቫይረሱ "የማይታይ" ሆኖ መቆየቱን እንዲያረጋግጡ ይደረጋል። በሕክምና ሳይንሱ አንድ ታካሚ ከመጀመሪያው የቫይረስ መጠን ምርመራ በኋላ ቢያንስ ለስድስት ወራት ቫይረሱ "የማይታይ" ሆኖ መቆየቱን ሊያረጋግጥ እንደሚገባው ያስቀምጣል። ይህን መሠረት በማድረግ ታካሚዎቹ በመጀመሪያ ስድስት ወር ላይ ምርመራ ያደረጉ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላም በየዓመቱ የቫይረስ መጠን ቆጠራውን / ቫይራል ሎድ / ምርመራ እያደረጉ ይገኛል። በተቋሙ ክትትላቸውን ከሚያደርጉት ታካሚዎች አብዛኛው የቫይረስ መጠን ልኬታቸው ማሽኑ ከሚያሳየው በታች ናቸው። የተቀሩትም ቢሆኑ በደማቸው የሚገኝ የቫይረስ መጠን የማይታይ ደረጃ ደርሷል። በዚህ ደረጃ መሆኑ ደግሞ የጤናቸውን ሁኔታ ጥሩ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህ በመሆኑ በተቋማችን ክትትል እያደረጉ የሚገኙ ታካሚዎች በአግባቡ የመድኃኒት ቁርኝታቸውን ጠብቀው የሚጓዘ በመሆናቸው፤ ከአስር ዓመት በላይ ጤናማ ሕይወትን እየመሩ ይገኛል።

**ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ**

በጤና ተቋማችን ክትትል የሚያደርጉት ታካሚዎቻችን ሁሌም የምንመክራቸው በመጀመሪያው ዓመት በደም ውስጥ የሚገኝ የቫይረስ መጠን የማይታይ ደረጃ ላይ ደረሰ ማለት፤ ከዚህ ከፍ አይልም ማለት እንዳልሆነ ነው። ምክንያቱም የመድኃኒት ቁርኝቱ ከተዛባና መድኃኒትን በአግባቡ መውሰድ ካልተቻለ የቫይረሱ መጠን /ቫይራል ሎዱ/ ይጨምራል። በሰውነት የሚገኝ ቫይረስ ከፍ አለ ማለት ደግሞ የሰውነት በሽታን የመቋቋም አቅሙ ይዳከማል፤ በተጓዳኝ በሽታ በቀላሉ ይጠቃል። ለተጨማሪ በሽታዎች ይዳረጋል። ሕመምተኛ ከሆነ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ብሎም ሥነ - ልቦናዊ ችግሮች በግለሰቡ ላይ ተጽእኖ ማሳደራቸው አይቀሬ ይሆናል። ስለዚህ በነዛ ተጽእኖ ውስጥ ያለ ሰው አምራች አይሆንም ፤ ጤናማ አይሆንም። ስለዚህ ታካሚው የጸረ - ኤች. አይ. ቪ. መድኃኒቱን በሰዓቱ የሕክምና ባለሙያው ባዘዘው መልኩ በአግባቡ ከመውሰድ በተጓዳኝ፤ በየዓመቱ የቫይረስ መጠን ቆጠራው ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል። በጤና ተቋማችንም በኩል ክትትል ለሚያደርጉ ታካሚዎች በየዓመቱ የቫይረስ ቆጠራው በማሽኑ ምርመራ ይደረግላቸዋል።

**እንደ መውጫ**

በአጠቃላይ የማይታይ መጠን የተገታ መተላለፍ መርሃ ግብር ተግባራዊ ሲደረግ አንዱና ትልቁ ኤች. አይ. ቪ. በደማቸው የሚገኝ ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ ነው። የመርሃ ግብሩ ትግበራ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ጤናማ ፤ አምራች ሆነው እስከ ሕይወት ዘመናቸው እንዲቆዩ ያደርጋል። ይህ በመሆኑ ለአገርም ለማህበረሰብም እንዲጠቅሙ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል። በተጨባጭ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው ቦሌ 17 ጤና ጣቢያ ክትትል እየተደረገላቸው ከሚገኙ ወገኖች ለመረዳት እንደተቻለው ኤች. አይ .ቪ. በደማቸው የሚገኝ ወገኖች በአግባቡ የጸረ - ኤች . አይ. ቪ. መድኃኒታቸውን መውሰድ ከቻሉ በደማቸው የሚገኝ የቫይረስ መጠን ወደ ማይታይ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ቫይረሱ ከማይታይበት ደረጃ በታች እንደሚሆን ጭምር ነው። ስለዚህ ኤች. አይ . ቪ. በደማቸው የሚገኝ ዜጎች መድኃኒትን በትክክል በመውሰድ ጤናማ ሕይወት ይኑሩ።

---

**ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ጋር በመተባበር በየሁለት ሳምንቱ የሚታተም**

# ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚፈጸምባቸው ሦስት ደረጃዎች

**ዳንኤል ዘነበ**

በዓለማችን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል የተደራጁ እና ድንበር ተሻጋሪ ከሚባሉ ወንጀሎች ይመደባል። በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ/ ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ማለት የተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች በማከናወን የሚገኝ ሀብትን/ ንብረትን በሕጋዊ መንገድ እንደተገኘ አስመስሎ ማቅረብ ነው። ወንጀለኞች በሕገ-ወጥ ሰዎች ዝውውር፣ በሕገ-ወጥ ምንዛሪ (ጥቁር ገበያ የውጭ አገራት ገንዘብ ምንዛሪ)፣ በሙስና፣ በኢንቨስትመንት ማጭበርበር፣ በታክስ ማጭበርበርና ምዝበራ ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት ያካብታሉ። በዚህ መልኩ ያካበቱት ሕገ ወጥ ሀብት ሕጋዊ መልክ በማላበስ ይጠቀማሉ።

ድርጊት እንደ ወንጀል መቆጠር የጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። በአሁኑ ወቅት ትልቅ ከሚባሉ ወንጀሎች ተርታ የተመደበ ሲሆን ወንጀሉ ለሀገር ደህንነት ስጋት ከሆኑ ሕገ ወጥ ተግባራት መካከል በዋነኝነት ተጠቃሽ ሆኗል። ይህ አይነቱ ወንጀል በተለይ በተለይ በአፍሪካ ከፍ ብሎ የሚታይ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚከታተለው ‹‹ግሎባል ፋይናንሻል ኢንተግሪቲ (ጂኤፍሲ) እና ሌሎችም ተቋማት የእያንዳንዱ አገር የገንዘብና የባንክ አሠራር ያለበትን ችግር፤ ሕጋዊ አሠራሮችና ሕጋዊ ያልሆነ የገንዘብ ዝውውርን ለመግታት የተዘጋጁ አሠራሮችን በመመርመር ይፋ የሚያደርጉ መረጃዎች የአህጉሪቱ ሀገሮች ለሙስና እና ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ክፍኛ ስለመጋለጣቸው ይመሰክራሉ። በዚህ ደረጃ በተለይ የአፍሪካ ፈተና የሆነው በሕገ-ወጥ መንገድ ገንዘብ የማሸሽ ወንጀል በአብዛኛው ጊዜ በሦስት ደረጃዎች ይፈጸማል፡፡

**ደረጃ 1 - አቀማመጥ**

በሕገ-ወጥ መንገድ ገንዘብ የማዘዋወር ወንጀል ሂደት የመጀመሪያው ደረጃ ተብሎ የሚመደበው በሕገወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ወደ ሌላ ማዘዋወር ወይም ማሰራጨት ነው። በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን በጊዜያዊነት ከእይታ ለማራቅ የሆነ ቦታ በማስቀመጥ የተገኘውን ገንዘብ በአነስተኛ ቁጥር በማከፋፈል ወደ ተለያዩ ባንኮች ማስገባት ወይም ገንዘቡን በቀላሉ በማይገኝበት ቦታ ደብቆ ለማስቀመጥ መሞከር ነው፡፡ ከዚህ በፊት ግን የተለያዩ የባንክ አካውንቶችን በመክፈት በትንሽ መጠን ይከፋፈላል። በዚህ መልኩ ከተከፋፈለ በኋላም በተለያየ መንገድ ወደ ስርጭት ውስጥ ይገባሉ። ይህ መሆኑ ሕገወጥ ገንዘቡን ማስቀመጥ በፋይናንስ ተቋማት እንዳይታወቅ የሚያደርገው ስለሆነ ለተቆጣጣሪ አካላት ገንዘቡን ለመከታተል በጣም አስቸጋሪ ያደርገዋል። አንዳንድ ጊዜ ጥሬ ገንዘብ ከሕገወጥ ገንዘቡ ምንጭ ከሆነው ሀገር ወደ ደካማ የፋይናንስ ደንብ ወደ ጥቂት ጥያቄዎች ወደሚቀርብባቸው አገሮች በድብቅ ይወሰዳል።

**ደረጃ 2 - መደራደር**

ሁለተኛው ደረጃ በመደራደር ገንዘቡን ከዋናው ምንጭ የበለጠ ለማራቅ ብዙ ጊዜ ማንቀሳቀስን ያካትታል። በሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል

> **በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄደውን ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሚከታተለው ‹‹ግሎባል ፋይናንሻል ኢንተግሪቲ (ጂኤፍሲ) እና ሌሎችም ተቋማት የእያንዳንዱ አገር የገንዘብና የባንክ አሠራር ያለበትን ችግር፤ ሕጋዊ አሠራሮችና ሕጋዊ ያልሆነ የገንዘብ ዝውውርን ለመግታት የተዘጋጁ አሠራሮችን በመመርመር ይፋ የሚያደርጉ መረጃዎች የአህጉሪቱ ሀገሮች ለሙስና እና ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ክፋኛ ስለመጋለጣቸው ይመሰክራሉ**

ውስጥ ታዋቂ ከሆኑ የመደራደሪያ ዘዴዎች ውስጥ ገንዘቡን ከአንድ ባንክ ወደ ሌላ ባንክ ማዘዋወር፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ገንዘቡን ከሀገር ውስጥ ማስወጣትና ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ የሎተሪ ወይም የቁማር ጨዋታ እድለኛ መስሎ መቅረብ፣ ገንዘቡን ከሌላ ሕጋዊ ሀብት ጋር መቀላቀል የመሳሰሉትን ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

**ደረጃ 3 - ውህደት**

በሕገ ወጥ መንገድ የገንዘብ ዝውውሩ የመጨረሻ ደረጃ በሕገ ወጥ መንገድ የተያዘውን ገንዘብ ወደ ሕጋዊ ምንጭ በመምሰል ወደ ዋናው ኢኮኖሚ መቀላቀልን ያካትታል። በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደተገለጸው በወንጀል ድርጊት የተገኘውን ሕገወጥ ገንዘብ ከተወሳሰበ እና በሕግ አስከባሪ አካላት በቀላሉ እንዳይገኝ እና እንዳይደረስበት ከተደረገ በኋላ ወደ ሕጋዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ማስገባት ነው፡፡ በዚህም በገንዘቡ የተለያዩ ድርጅቶችን በመክፈት ማስፋፋት፣ ሕንፃ መገንባት፣ አክሲዮኖችን መግዛት፣ የሪል ስቴት ቤቶችን መግዛት እና የቅንጦት እቃዎችን መግዛት የመሳሰሉት ያካትታል፡፡ በዚህ መልኩ ወንጀለኞቹ ጥብቅ የድርጅት ምስጢር ሕግ ባለባቸው ሀገራት ግንባር ቀደም ኩባንያዎችን ማቋቋም ይችላሉ። ከዚያም ወንጀለኞቹ ማንነታቸውን እየጠበቁ ገንዘቡን ማግኘት ይችላሉ።

በዚህ መልኩ የሚፈጸም ወንጀል የሀገር የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዳይረጋጋ በማድረግ እንደዚሁም በንብረቱ/ በገንዘቡ ሌሎች ወንጀሎች እንዲፈጸሙ ድጋፍ በማድረግ የአንድ ሀገር ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ወንጀሉን ለመከላከል ሁሉም የባለድርሻ አካላት በጋራ ሊሠሩ ይገባል ።

# ስፖርት



# በቆጂን እንደስሟ ለማግዘፍ የሚተጉ ወጣቶች

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እምብርት የሆነችው በቆጂ በታሪክ መዛግብትና ከአትሌቲክስ ቤተሰቡ ልብ በማይለቅ የወርቅ ቀለም ስሟ ቢሰፍርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአትሌቲክስ እንቅስቃሴዋ መቀዛቀዝ እየታየ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ። በቆጂ በርካታ አትሌቶችን በስፖርቱ አንጻር ለዓለም መድረክ ታብቃ እንጂ ከማህጸኗ የወጡት የዓለም ከዋክብት ግን ውለታዋን እንዳልከፈሏት ቅሬታ የሚያሰሙ ጥቂት አይደሉም። በአንጻሩ ለስፖርቱ ፍቅር ያላቸው እና አትሌቲክስ በደማቸው የሚዘዋወር የስፖርቱ ወዳጆች በቁጭት ተነሳስተው የቻሉትን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ከእነዚህ መካከል አንዱ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ የተሰማራው ወጣት አንዷለም ጌታቸው ነው። በቆጂ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ አትሌቶችን ያወጣች፤ ነገር ግን የስሟን ያህል መግዘፍ ያልቻለች ትንሽ ከተማ መሆኗን ይጠቁማል። መንግስትን ጨምሮ ከበቆጂ ተነስተው ዝነኛ የሆኑ አትሌቶችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚገባትን ያህል ድጋፍ ሊያደርጉላት አልቻሉም። ከዚህ ቁጭት በመነሳትም በቆጂን ለማስተዋወቅ ዘርፈ ብዙ ጥረት ከማድረግ ባለፈ ለአምስት ጊዜያት የ5 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫዎችን አዘጋጅቷል። የመሮጫ ቲሸርቶችን በነጻ በማቅረብ ህዝቡን የሚያሳትፍ ሲሆን፤ ይህንንም የሚያደርገው ስፖርቱን ለማነቃቃት እንደሆነ ይናገራል።

አንዱዓለም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውጤት ለመቀነሱ አንድ ምክንያት በቆጂ እንደቀድሞው አትሌቶችን ማፍራት ባለመቻሏ እንደሆነም እምነቱ ነው። ለማሳያም ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ካስመዘገበቻቸው 23 የወርቅ ሜዳሊያዎች መካከል 11 የሚሆኑት ከበቆጂ በፈለቁ አትሌቶች የተመዘገቡ መሆናቸውን ያስቀምጣል። በአንጻሩ ከቅርብ ጊዜያት በኋላ ይህ ቁጥር እየቀነሰ ነው። በቆጂ ላይም በማሰልጠኛ ማዕከላትና በግላቸው ጥረት ከሚያደርጉት ውጪ እንደመንግስት የተደረገ ጥረት ነገር የለም።



ወጣቷ አሰልጣኝ ፈቲያ አብዲ ሳለፉት ሰባት ዓመታት የበቆጂን ታዳጊዎች እያሰለጠነች ትገኛለች፣

የበቆጂ አትሌቶች ሙዚየም ለመገንባት ከ18 ዓመታት በፊት መሰረተ ድንጋይ ይጣል እንጂ እስካሁን እውን መሆን አልቻለም። በ1996 ዓ.ም የተገነባው የበቆጂ ስታዲየምም እስካሁን መም ሊነጠፍለት ቀርቶ የአሸዋ መሮጫ ለማድረግም አልተቻለም። እስካሁንም ድረስ አትሌቶች ስልጠና የሚያደርጉት ከእንስሳት ጋር እየተጋፉ መሆኑን ወጣቱ ይጠቁማል። ከ200 በላይ ኢንተርናሽናል አትሌቶችን ያፈራቸውን በቆጂ ሌላው ዓለም ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ቀጥሎ የሚያውቀው ብቸኛው ስፍራም ናት። በመሆኑም በየመድረኩ በቆጂ የአትሌቶች ምንጭ መሆኗን ከመናገር ባለፈ ሊሰራበት ይገባል ባይ ነው። እንደ ኬንያዎቹ የአትሌት መፍለቂያ ከተሞች የተደራጀና ዘመናዊ የሆነ የማሰልጠኛ እንዲሁም ውድድር የሚካሄድባቸው የማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲኖራት ሁሉም እንደየድርሻው መስራት እንዳለበትም ያስቀምጣል።

ሌላኛዋ በቆጂን ወደ አትሌቲክስ ምንጭነቷ ለመመለስ በቁጭት ተነሳስታ ጥረት የምታደርገው ወጣት ፈቲያ አብዲ ናት። ወጣቷ እንደነ ጥሩነሽ ዲባባ እና ቲኪ ገላና ካሉ አትሌቶች ጋር አትሌቲክስን የጀመረች ቢሆንም በህመም ምክንያት የአትሌትነት ህይወቷ ሊቀጥል ባለመቻሉ ወደ አሰልጣኝነቱ ገብታለች። ላለፉት ሰባት ዓመታትም በዚሁ ስራ ላይ ተሰማርታ ትገኛለች። ስልጠናው «ሲንቄ» በተባለ ሃገር በቀል የእርዳታ ድርጅት የሚደገፍ ሲሆን፤ በዚህ ወቅት 80 ታዳጊ አትሌቶች እየሰለጠኑ ይገኛሉ። በዚህ የስልጠና ፕሮጀክት ውስጥ ለሶስት ዓመት በስልጠና ላይ የሚቆዩ ታዳጊዎችም እድሜያቸው ከ15-18 የሚሆኑ ናቸው። በዚህ ፕሮጀክት ላይ በማሰልጠኛ ላይ ከሚገኙት ታዳጊዎች መካከል የተሻለ ተስፋ በማሳየት በርካቶቹ በበቆጂ አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል እንዲሁም በጥሩነሽ ዲባባ አካዳሚ ተመልምለው በመሰልጠን ላይ ይገኛሉ።

በቆጂ ከዚህ ቀደም በነበረችበት ሁኔታ አትሌቶችን እያፈራች አይደለም ለሚለው ሃሳብ ድጋፍ እንጂ አትሌቶች እንዳልጠፉ ወጣቷ አሰልጣኝ ትገልጻለች። በርካቶች ከገጠራማ አካባቢዎች ጭምር በመምጣትና ቤት በመከራየት የሚሰሩ ቢሆንም የስልጠና ቁሳቁስ ድጋፍና እገዛ የሚያደርግላቸው የለም። በዚህ ምክንያት እንደከዚህ ቀደሙ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ከቁሳቁስ ድጋፍ ባለፈ ከአካባቢው የፈለቁ ታዋቂ አትሌቶች የሞራል ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ትጠይቃለች። እርሷን ጨምሮ ሌሎች በስፖርቱ ፍቅር ተነሳስተው እየተጉ ያሉ አሰልጣኞችም ከስልጠናው ጎን ለጎን ምክሮችን በመለገስ እንዲሁም ተምሳሌት የሚሆኗቸውን አትሌቶች ታሪክ በመንገር ውጤታማ እንዲሆኑ በማበረታታት ለወደፊት ህይወታቸው ተስፋ እንዲሰንቁ እያደረጉ መሆኑንም ታስረዳለች።


## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

የአመልካች ስም እና አድራሻ

ሃንግዡ ሂክሚክሮ ሴንሲንግ ቴክኖሎጂ ሲኦኤልቲድ

Hangzhou Hikmicro Sensing Technology Co.Ltd) አድራሻ Building A1, No.299, Qiushi Road, Tonglu Economic Development Zone,Tonglu Country, Hangzhou 311501,China

የንግድ ምልክቱ ስዕላዊ መግለጫ:- የምስል

| | ማመልከቻ ገቢ የሆነበት ቀን | የማመልከቻ ቁጥር |
|---|---|---|
| | 27/01/2022 | FTM/13128/22 |

ዓለም አቀፍ ምድብ:-09፣42

ማመልከቻ የሚሸፍናቸው ምርቶች

**ምድብ 09፡-** የኮምፒውተር ማህደረ ትውስታ መሳሪያዎች፤ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች፣ ሪከርድ፤ የኮምፒውተር ኦፕሬቲንግ ፕሮግራም፣ ሪከርድ፤ የኮምፒውተር ሶፍትዌር፣ ሪከርድ፤ የኮምፒውተር ሶፍትዌር መተግበሪያዎች፣ ዳውንሎዴብል፤ ፓርኪንግ ሜትር፤ የፍተሻ ማመሳከሪያ መሳሪያ፤ ተመሳስለው የተሰሩ ሳንቲሞች መመርመሪያ፤ በሳንቲም የሚሰራ መሳሪያ፤ ሆሎግራም፤ የፊት ለይቶ ማወቂያ መሳሪያ፤ አቴንዳንስ ማሺን፤ ፎቶቴሌግራፍ መሳሪያ፤ መለኪያ መሳሪያ፤ የኤሌክትሮኒክስ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች፤ የመግባቢያ መሳሪያዎች፤ ቪድዮ ቴሌፎንስ፤ አለምአቀፍ አቅጣጫ መጠቆሚያ (GPS) መሳሪያ፤ ኮምፓክት ዲስክስ(ኦዲዮ-ቪዲዮ)፤ የድምፅ መቅረጫ መሳሪያ፤ የቪዲዮ መቅረጫ፤ መከታተያ ካሜራ፤ ለህክምና ላልሆኑ አላማዎች ክትትል መሳሪያ፤ የህፃናት ደህንነት መቆጣጠሪያ፤ ካሜራ(ፎቶግራፊ)፤ ለህክምና ላልሆኑ አላማዎች ማጣሪያዎች፤ለካሜራ ትሪፖድስ፤ለመነፅር መከለያዎች፤ ሰልፊ ስቲክ( በእጅ የሚያዙ ሞኖፖዶች)፤ የመለኪያ መሳሪያዎች፤ኦፕቲካል ሌንስ፤ ፋይበር [fibers (Am.]፤ኦፕቲክ ኬብል፤ የኤሌክትሪክ ሽቦ፤ ገመድ፤ ለተቀናጀ ፍሰት የሚረዳ ዋፈር፤ ችፕስ(Integrated Circuits)፤ ካፓሲቶርስ፤ የቪዲዮ ማሳያዎች፤ የርቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያ፤ ብርሃን የሚያሳዩ ክሮች[ኦፕቲካል ፋይበርስ[ፋይበርስ]]፤ ለኢንዱስትሪ ስራ ለርቀት መቆጣጠሪያ የሚያገለግሉ የኤሌክትሪክ እቃዎች፤ የመብረቅ መቆጣጠሪያ፤ እሳት ማጥፊያ፤ ለኢንዱስትሪ ስራ የራዲዮሎጂ ማሳያዎች፤ የአደጋ መከላከያ መሳሪያ፤ ስርቆት መከላከያ መግጠም፣ ኤሌክትሪክ፤የፀረ-ስርቆት ማስጠንቀቂያ መሳሪያ፤ ባትሪዎች፣ ኤሌክትሪክ፤ ስላይድስ (ፎቶግራፊ)፤ ሴንሰርስ፤ ጠቋሚዎች፤ የኢንፍሬርድ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ፤ ተርማል ኢሜጂንግ የሙቀት መለኪያ መሳሪያ፡፡

**ምድብ 42፡-** ሳይንሳዊ ምርምር፤ ምርምር እና አዳዲስ ምርቶችን ለሌሎች ማሳወቅ፤ የኮምፒውተር ሶፍትዌር ንድፍ፤ በሶፍትዌር ህትመት ማዕቀፍ ውስጥ የሶፍትዌር ልማት፤ የኮምፒውተር ስርዓት ንድፍ፤ የኮምፒውተር ኪራይ፤ የኮምፒውተር ሶፍትዌር ኪራይ፤ የኮምፒውተር ፕሮግራም፤ ኮምፒውተር ሶፍትዌር መጫን፤ ኮምፒውተር ሶፍትዌር ጥገና፤ መረጃን ወይም ሰነዶችን ከአካላዊ ወደ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መቀየር፤ የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን እና ዳታ መቀየር(Not Physical Conversion)፤ የኮምፒውተር መረጃ ሪከቨሪ፤ የኮምፒውተር ስርዓቶች ትንተና፤ ለሌሎች ድረ-ገፆችን መፍጠር እና ማቆየት፤ ሆስቲንግ ኮምፒውተር ሳይትስ (ድረ-ገፅ)፤ ሰርቨር ሆስቲንግ፤ የኮምፒውተር ቫይረስ መከላከያ ሰርቨር፤ የኮምፒውተር ስርዓቶችን በርቀት መከታተል፤ የቴክኒክ ፕሮጀክት ጥናቶች፤ ምህንድስና፤ የዳሰሳ ጥናት፤ የከተማ ፕላን፤ ሜካኒካል ምርምር፤ የኢንዱስትሪ ንድፍ፤ የኮምፒውተር ሃርድዌር ዲዛይን እና ልማት በተመለከተ የማማከር አገልግሎት፤ የኮምፒውተር ቴክኒክ ማማከር፤ ሶፍትዌር እንደ አገልግሎት[SaaS]፤ ፕላትፎርም እንደ አገልግሎት[PaaS]፡፡

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ከተዘረዘሩት ዕቃዎች ጋር በተያያዘ ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃውሞ ያለው ሰው የጋዜጣ ማስታወቂያ በወጣ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ካላቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ባለቤቱ ሳይፈቅድ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክቱን ቢገለገል ወይም ባለቤቱ በንግድ ምልክቱ ላይ ያለውን ማንኛውም ዓይነት መብቱን የሚጋፋ ተግባር ሲፈጽም ቢገኝ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ክስ እንደሚመሰረትበት እናሳውቃለን፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-285 15/10/2014 (22/6/2022)

POPULATION MEDIA CENTER
Acting for Change

# ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# እጅ መታጠብ ለጤናማ አኗኗር

በዓለማችን በአግባቡ እጃቸውን የሚታጠቡ ሰዎች ቁጥር ሃያ በመቶ ሲሆኑ በሀገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ አምስት በመቶ ብቻ ናቸው:: እጃችንን መታጠብ ያለብን ለሃያ ሰከንድ መሆን ሲገባው አብዛኛው ማህበረሰብ ግን ለ6 ሰከንድ ያህል ብቻ የሚታጠብ መሆኑ የችግሩ አሳሳቢነት ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ::

በተጨማሪም እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር የ2019 የዩኒሴፍ (UNICEF) ሪፖርት እንደሚያመለክተው በዓለማችን 40 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ብቻ የተሟላ የእጅ መታጠቢያ ቁሳቁስ ያለው ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ስምንት በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ብቻ ነው የተሟላ የእጅ መታጠቢያ ቁሳቁስ ያለው:: 92 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ የእጅ መታጠቢያ ቁሳቁስ የለውም:: አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በገጠራማው የሀገሪቱ ክፍል የሚኖር በመሆኑ ከተማ ከሚኖረው ማህበረሰብ ይልቅ የቁሳቁስ እጥረቱ ያጋጥመዋል::

ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ተመርኩዞ የዓለማችንም ሆኑ የሀገራችን ሕዝቦች በቀላሉ ለተቅማጥ፣ ለኮሮና፣ ለታይፎይድ፣ ለትራኮማና ለሌሎችም ተላላፊ በሽታዎች ይበልጥ ተጋላጭ መሆናቸውን መገመት አያዳግትም:: እጅ መታጠብ ለጤናማ አኗኗር በሚል የተሠራው መረጃ በደቡብ ክልል ጌዲዮ ዞን ቡሌ ወረዳ ሲካ ቀበሌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው:: የዚህ ቀበሌ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት አራት ሺ587 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ሁለት ሺ 248 ወንዶች እንዲሁም ሁለት ሺ 334 ሴቶች ናቸው::

በዚህ ትምህርት ቤት በተካሄደው ቃለ ምልልስ የተካተቱት የትምህርት ቤቱ ዋና ርእሰ መምህር አቶ ዘውዴ እና የትምህርት ቤቱ የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ ተጠሪ አቶ ሰለሞን ናቸው:: መረጃው የተሰበሰበበት ዓላማ ፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ ከቡሌ ወረዳ ጤና ጽሕፈት ቤት እና ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር እየሠራ ያለውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ የባህሪ ለውጥ ተጽእኖና አዎንታዊ ጎኑን ለመለየትና የፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃውን ለመገምገም ነው::

### ከማኅበረሰብ ንቅናቄ በፊት የነበሩ ችግሮች

የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር አቶ ዘውዴ “ፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ እጅ መታጠብን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በትምህርት ቤቱ ጤናን በተመለከተ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ነበሩ” ይላሉ:: ከእነዚህም መካከል በመሠረታዊነት እጅን በአግባቡ መታጠብን ልምድ አለማድረግ፣ ሽንት ቤቶች ቢኖሩም የሴትና የወንድ ተብለው በጾታ አለመለየታቸው፣ ከሽንት ቤት መልስ እጅን በአግባቡ ለመታጠብ የሚያስችሉ የእጅ መታጠቢያ ሳሙናና ውሃ አለመዘጋጀታቸው ወሳኝ የሆኑ ሰባቱ የእጅ መታጠቢያ ጊዜያትና የእጅ አስተጣጠብ ደረጃዎች ግንዛቤ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ ዋነኛ ችግሮች መሆናቸውን ይገልጻሉ:: ከዚህ በተጨማሪም የሽንት ቤት አጠቃቀም በተገቢው መንገድ የሚከናወን አለመሆኑ (የሽንት ቤቱ ወለል ላይ የተዝረከረከ ዓይነ ምድር ማየት የተለመደ መሆኑ)፣ የተደረመሰ ሽንት ቤት አለመታደሱ ወይም አለመታሸጉ የመሳሰሉት ጎልተው የወጡ ችግሮች መሆናቸውን ዋና ርዕሰ መምህሩ አስረድተውናል::

### በኅብረተሰብ ንቅናቄው የተሠሩ ሥራዎች

ችግሩን ለመቅረፍ ስለተሠሩ ሥራዎች የክበቡ ተጠሪ አቶ ሰለሞን እንደተናገሩት፤ የቡሌ ወረዳ ጤና ጽሕፈት ቤት ከዩኒሴፍና ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ለተማሪዎች ቅድመ ስልጠና በመስጠትና እያዝናኑ የሚያስተምሩ መልዕክቶችን በማካተት ስለሰባቱ ወሳኝ የእጅ መታጠቢያ ጊዜያትና የአስተጣጠብ ደረጃዎች ለተማሪዎች፣ለመምህራንና ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሠራተኞች በተግባር የተደገፈ ትምህርት ተሰጥቷል:: ግንዛቤውን ለመፍጠር አጭር ጭውውት፣ ግጥምና ተግባራዊ ማስተማሪያ ዘዴዎች ሥራ ላይ ውለዋል::

“የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሙ ዓላማ እጅ መታጠብን የትምህርት ቤቱ አባላት ለራሳቸው በመተግበር፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለማህበረሰቡ እንዲያስተላልፉና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም ማህበረሰቡን ከተቅማጥና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች እንዲጠብቅ የሚያግዝ ነበር” ብለዋል::

### ፕሮግራሙ ያሳደረው በጎ ተጽእኖ

ከፕሮግራሙ የተገኘው ለውጥ አስመልክቶም ፈጣን ለውጥ መገኘቱን አቶ ዘውዴ ተናግረዋል:: “የተገኘው ለውጥ ፈጣን ነው:: ዋና ዋናውን ለመጥቀስ ያህልም ከሽንት ቤት መልስ የእጅ መታጠቢያ ውሃና ሳሙና የተዘጋጀ መሆኑን፣ተማሪዎችና መምህራን ከሽንት ቤት መልስ እጃቸውን በውሃና ሳሙና መታጠብ መጀመራቸውንና የተደረመሰ ሽንት ቤት መታሸጉን” ብለውናል:: ሽንት ቤቶች በጾታ መለየታቸውን፣ ሽንት ቤት ወለል ላይ የሚታይ ዓይነ ምድር መወገዱን፣ ከግንዛቤ ማስጭበጫ ፕሮግራሙ በኋላ መጸዳጃ ቤትን በአግባቡ የመጠቀም ልምድ እየዳበረ መምጣቱንና በርካታ ለውጦች መኖራቸውንም የክበቡ ተጠሪ አቶ ሰለሞን አስረድተውናል::

ሰባቱን ወሳኝ የእጅ አስተጣጠብ ደረጃዎች ለአንባቢያን ግልጽ ይሆኑ ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሥዕላዊ መግለጫ የተመለከተ ሲሆን፣ ሁሉንም ተግባራዊ ለማድረግ የበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ እራሳችንን፣ ቤተሰባችንንና ማህበረሰባችንን ከተላላፊ በሽታዎች እንከላከል::

### ሰባቱ የእጅ አስተጣጠብ ደረጃዎች




- **የፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ:**
  - Website (Search): https://www.pmcethiopia.org/
  - Facebook(Search): www.facebook.com/populationmediacenterethiopia
  - You Tube (Search): PMC ETHIOPIA
  - በፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ የሚዘጋጀውን ንቃቃት ተከታታይ የራዲዮ ድራማ ለመከታተል:-

ነቃቃት Nekakat

  - Website(Search): https://pmcethiopia.org/pages/nekakat-radio-serial-drama/
  - Facebook(Search): www.facebook.com/nekakatradiodrama
  - You Tube (Search): NEKAKAT
  - Telegram (Search): https://t.me/NEKAKAT_RSD
  - በፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር-ኢትዮጵያ የሚዘጋጀውን ያላለቀ ጉዞ የራዲዮ ፕሮግራም ለመከታተል:-

ያላለቀ ጉዞ Yalaleke Guzo

  - Website(Search): https://pmcethiopia.org/pages/yalaleke-guzo/
  - You Tube (Search): PMC ETHIOPIA
  - Telegram (Search): https://t.me/yg_pmc

# ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## የምሥራቅ አፍሪካ አገራት የደመቁበት የጥበባትና ባህል ፌስቲቫል

**ሶሎሞን በየነ**

የምሥራቅ አፍሪካ የጥበባት እና የባህል ፌስቲቫል “ጥበባትና ባህል ለቀጠናዊ ትስስር” በሚል መሪ ቃል ከሰኔ 07 እስከ 12/2014 ዓ.ም በአፍሪካ መናገሻ ከተማ አዲስ አበባ ተካሂዷል። በፌስቲቫሉ የዩጋንዳ፣ የቡሩንዲ፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያ፣ የኬኒያ ወ.ዘ.ተ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት እንዲሁም የክልል እና የከተማ አስተዳደር የኪነጥበባትና የባህል ልዑክ ቡድን ታድመዋል፡፡ ፌስቲቫሉም በተያዘለት መርሃ ግብር መሠረት የመክፈቻ ፕሮግራሙን ጨምሮ ለስድስት ቀናት በተለያዩ ፕሮግራሞች ሲካሄድ ቆይቶ ያሳለፍነው ዕሁድ ፍጻሜውን አግኝቷል።

በፌስቲቫሉ ምንም ምን መርሃ ግብሮች እንደተካሄዱና ፌስቲቫሉ ከተዘጋጀበት ዓላማ አኳያ ምን ያህል ግቡን መቷል በሚሉት ላይ በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ጌታቸው የሰጡንን ማብራሪያ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

ፌስቲቫሉ የመክፈቻ ፕሮግራሙን ጨምሮ በአራት ቦታዎች ለስድስት ቀናት ያህል በተለያዩ ፕሮግራሞች ሲካሄድ መቆየቱን ዳይሬክተሩ አውስተው፤ ትልቁና የመጀመሪያው የመክፈቻ ሥነሥርዓት ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት እስከ መስቀል አደባባይ በሚዘልቅ በደማቅ የባህልና ጥበባት የጎዳና ላይ ትርዒት የተጀመረ ሲሆን፤ በትዕይንቱ ደማቅ የባህላዊ ክንዋኔዎችና የሰርከስ ትርዒት ታይቷል። በጣም በርካታ የመዲናዋ ነዋሪ ይሄንን ትርኢት ተመልክቷል። ቸርቸር ጎዳና በዚህ ትርኢት ደምቃም ነበር። በባህላዊ ክንዋኔዎችና የሰርከስ ትርዒት የደመቀው የጎዳና ላይ ትርኢቱ ቀጥታ ወደ መስቀል አደባባይ አቅንቶ በዚያም ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮችና የተለያዩ ሀገሮች አምባሳደሮች በተገኙበት የኤግዚቢሽንና የሙዚቃ ፌስቲቫል በይፋ ተከፍቷል።

በኤግዚቢሽኑ በጥቅሉ የቀረቡት የዕደ ጥበብ ውጤቶች



**አቶ አለማየሁ ጌታቸው፤**

ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ የሸክላ፣ የቀርከሃ፣ የሸመና እና የእንጨት ሥራ ውጤቶች እንዲሁም ከሳር የሚሠሩ ልዩ ልዩ የስፌት ዓይነቶች ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው ለዕይታ ቀርበዋል። ተሳታፊ ሀገራት በተለይ ዩጋንዳና ኬኒያ የዕደጥበብ ሥራዎችን ለዕይታ አቅርቦ ከማስጎብኘት ባለፈ ለሽያጭ አቅርበዋል። በዚህም የፌስቲቫሉ ታዳሚዎች የሌሎች አገሮችን የዕደ ጥበብ ውጤቶችን መሸመት ችለዋል። ሌላው በከተማዋ የሚገኙ ትልልቅ ሆቴሎች እና ሬስቶራንቶች የተለያዩ አካባቢዎችን የሚወክሉ ባህላዊ ምግቦቻችን ባህላዊ ጣዕማቸውንና ይዘታቸውን ሳይለቁ አዘጋጅተው ለዕይታ አቅርበዋል።

እንዲሁም በመድረኩ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የተለያዩ ባህላዊ ትዕይንቶችን አቅርበዋል። በተመሳሳይ የመድረኩ ተሳታፊ ሀገራትም አቅርበዋል። የብዙ አገራት አምባሳደሮች፣ የተለያዩ የአገር ውስጥና ለተለያዩ ዓላማ የመጡ የውጭ ጎብኚዎች ወይም እንግዶች ኤግዚቢሽኑን ጎብኝተዋል። በተለይ ማታ ማታ በርከት ያለ የከተማዋ ነዋሪ በኤግዚቢሽኑ ተገኝቶ ጉብኝት ሲያደርግም ነበር። በመድረኩም ታዋቂ የሀገሪቱ ዘፋኞች ሙዚቃዎች ቀርበዋል። በኤግዚቢሽኑ የመክፈቻ ሥነሥርዓት የያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት ለመርሃ ግብሩ ተብሎ የተዘጋጀ ህብረ ዝማሬ ያቀረበ ሲሆን፤ በዚህም በአፍሪካ የሚታወቁ ህብረ ዝማሬዎችን ለታዳሚዎች ማቅረቡን ተናግረዋል።

ዳይሬክተሩ፤ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የጥበባት እና ባህል ፌስቲቫል አካል የሆነው የስዕል እና ቅርጻ ቅርጽ ኤግዚቢሽን በእንጦጦ ሙዚየም በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል። በአውደርዕይው የተለያዩ ስዕሎችና ቅርጻቅርጾች ከመቅረቡ ባሻገር የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሀገር በቀል ዕውቀትን በመጠቀም እንዴት በባህላዊ ዘዴ ብረት ማቅለጥ እንደሚቻል አሳይተዋል። አውደርዕዩ የምሥራቅ አፍሪካ ሥነ-ጥበባት እሴቶችን ለማስተዋወቅ እና በአርቲስቶች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ትስስር ለማሳደግ ጥሩ አጋጣሚ የፈጠረ እንደነበር ይናገራሉ።

ሌላው የፌስቲቫሉ አንዱ አካል የነበረው የፊልም ፌስቲቫል እንደነበር ዳይሬክተሩ ገልጸው፤ በፊልም ፌስቲቫሉ የመክፈቻ ሥነሥርዓት በ1957 ዓ.ም በኢትዮጵያዊ ደራሲና ፕሮዲዩሰር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው “ሕይወት አባቷ ማነው?” የተሰኘው የአማርኛ ፊልም ለኅብረተሰቡና ለተጋባዥ እንግዶች ለዕይታ ቀርቧል። ከዚህ በተጨማሪ በፊልም ፌስቲቫሉ በስክሪን/ በሲኒማ ቤት በመታየት ላይ ያሉ የተመረጡ ፊልሞች ለኅብረተሰቡ ቀርበው በፊልሞቹ ላይ ውይይት ተደርጎባቸዋል። በተዘጋጀው የፊልም ፌስቲቫል የመክፈቻ ሥነሥርዓት ላይ የፊልም ኢንዱስትሪን በምሥራቅ አፍሪካ በማስፋፋት በርካታ የሥራ ዕድሎችንና የገቢ ማግኛ መንገዶችን በቀጠናው መፍጠር እንደሚገባ እንዲሁም በዘርፉ ካለው እምቅ ዕውቀትና ሀብት ለመጠቀም የቀጠናው አገራት በአንድነት መሥራት እንደሚገባቸው ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት ማሳሰባቸውን ተናግረዋል።

እንዲሁም የፌስቲቫሉ አካል የሆነው የጥበባትና ባህል ዐውደ ጥናት ተካሂዷል። የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በተፈጥሯዊ አቀማመጥ የተሳሰሩ፣ ባህልና ቋንቋን የሚጋሩ ሕዝቦች ያሏቸው ሀገራት ናቸው፡፡ የሕዝቦችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ለማቀራረብ የሚያስችሉ ነባራዊ ምቹ ሁኔታዎችን የሚጠቁሙ አራት ጥናቶች በዐውደ ጥናቱ ቀርበዋል፡፡ በቀረቡት የመነሻ ሃሳቦች ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለስልጣናት፣ የተለያዩ አገሮች አምባሳደሮችና ልዑካን ቡድኖች በተገኙበት ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

በውይይቱም የምሥራቅ አፍሪካ ቀጠና አብዛኛው የምዕራቡና የምሥራቁ ዓለም ሀገራት ልዩ ፍላጎት ያለበት ቀጠና በመሆኑ የቀጠናውን የእርስ በእርስ ግንኙነት በማጠናከር የቀጠናው ሕዝቦች በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ልማቶች ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚጠበቅ፤ እንዲሁም አፍሪካን አንድ ለማድረግ የቀጠናዊ ትስስሩ መጠናከርና መጣጣም እንዳለበት ከመድረኩ ጎልቶ ተነስቷል። እርስ በእርስ ለመግባባትና የቀጠናውን ትስስር ለማጠናከር ቋንቋ ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነም ተመላክቷል። ለዚህ ደግሞ ድንበር ተሻጋሪ ቋንቋዎችን ከማልማት ባሻገር በምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ ከፍተኛ ስርጭትና ብዙ ተናጋሪ ያለው “ሱኋሊ” ቋንቋን የበለጠ መጠቀምና ማልማት ቀጠናዊ ብሎም አፍሪካዊ ትስስሩን የበለጠ እንደሚያጠናክረው በመድረኩ ተገልጿል።

በዚህ ላይም ከፍተኛ ውይይት ተደርጎበት “አፍሪካን ነፃ ማውጣት ካለብን የራሳችን የምንግባባቸው የጋራ ቋንቋ ያስፈልጉናል” የሚል ድምዳሜ ላይ በጉባኤው ተደርሷል። ይህ በከፍተኛ አመራሮች ውሳኔ ተሰጥቶበት የፖሊሲ አቅጣጫ ተቀርጾለት ወደፊት ወደ ትግበራ ጉዳይ የሚገባ ስለሆነ በሂደት ውጤቱ የሚታይ ይሆናል። በዚህ ጉዳይ ላይ የሀገራቱ የባህል፣ ኪነጥበብና ስፖርት እንዲሁም ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተገናኝተው የሚወያዩበት ይሆናል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ የመርሐ ግብሩ አካል እና የፌስቲቫሉ ማጠቃለያ የሆነው የአምስት ኪሎ ሜትር ሩጫ ውድድር መካሄዱን ጠቁመው፤ ውድድሩ የበለጠ ፍቅርን ፣ አንድነትን እና ሰላምን ለማጠናከርና አወንታዊ የፉክክር መንፈስ ለመፍጠር ፋይዳው የጎላ ነበር። በአጠቃላይ ፌስቲቫሉ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን ግንኙነት በጥበብና በባህል በማስተሳሰር ሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል እርሾ የተጣለበት መድረክ እንደነበር ዳይሬክተሩ ገልጸዋል።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia